# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት




## የብሔራዊ የእንስሳትና ጤና ጥበቃ ኢንስቲትዩት

## የእንስሳት ክትባትና ሪኤጀንቶችን ማምረት፣ መድኃኒቶችን የማቀነባበር እና የአያያዝ ሥርዓት አፈፃፀምን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

መጋቢት 2010

አዲስ አበባ

## ማውጫ

ማውጫ ........ i
የክዋኔ ኦዲቱ ዋና ዋና ግኝቶችና ማሻሻያ ሃሳቦች ማጠቃለያ (Executive summary) ........ I
ክፍል አንድ ........ 1
መግቢያ ........ 1
የብሔራዊ እንስሳት ጤና ጥበቃ ኢንስቲትዩት ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ አላማ ........ 2
የብሔራዊ ጤና ጥበቃ እንስቲትዩቱ ስልጣንና ተግባር፡- ........ 2
የኢንስቲትዩቱ ደርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል፡ ........ 3
የፋይናንስ ምንጭ፡- ........ 3
የኦዲቱ ዓላማ፡- ........ 5
ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ ........ 5
የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) እና መመዘኛ መስፈርት ........ 5
የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ ........ 5
የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች ........ 6
የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ........ 6
የኢንስቲትዩቱ የአሰራር ሥርዓት መግለጫ (Process description) ........ 6
ክፍል ሁለት ........ 7
የኦዲት ግኝቶች ........ 7
የክትባቶች አመራረት ቴክኖሎጂ ቀልጣፋና ዉጤታማ መሆኑን በተመለከተ፡- ........ 7
የደንበኞች ፍላጎት ያገናዘበ የክትባት ምርት በዓይነት፣ በመጠንና በጊዜ ማቅረብን በተመለከተ፡- ........ 13
ሪኤጀንቶችን የማምረትና መድኃኒቶችን የማቀነባበር ሥራ ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፡- ........ 16
የሚመረቱት የክትባት ምርቶች ጥራቱ፣ ደህንነቱና ፍቱንነቱን በተመለከተ፡- ........ 18
ኢንስቲትዩቱ በክትባት አያያዝና አጠቃቀም ዙሪያ ለተጠቃሚዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ማከናወኑን በተመለከተ፡- ........ 20
የክትባት ምርት እድገት ማፋጠንን፣ ማስፋፋትንና ማሻሻልን በተመለከተ፡- ........ 24
የሚመረቱት ክትባቶች የሃገሪቱን ፍላጎት አሟልቶ ወደ ውጭ መላካቸውን በተመለከተ፡- 25
ክትባቶች ሲመረቱም ሆነ ከተመረቱ በኃላ የምርት ብክለትና ብክነት ሣይኖር ጥራታቸውን ጠብቀው ለተጠቃሚ መድረሳቸውን በተመለከተ፡- ........ 27
ንብረቶች ሲበላሹ ቶሎ ተጥግነዉ ወደ ሥራ የሚገቡ መሆኑን በተመለከተ፡- ........ 29

የአካባቢና የባለሙያ ደህንነት የሚጠብቅ የአሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፡- ....... 30
የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ክፍተትን በመለየት ለባለሙያዎች ስለጠና መሰጠቱን በተመለከተ፡- ....... 31
ክፍል ሶስት ....... 33
የመደምደሚያ ሃሳቦች ....... 33
ክፍል አራት ....... 36
የማሻሻያ ሃሳቦች ....... 36
አባሪ- 1 ፡የኢንስቲትዩቱ መዋቅራዊ አደረጃጀት መግለጫ፡- ....... 40
አባሪ 2፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria ....... 41
አባሪ 3፡ በኢንስቲትዩቱ የሚመረቱ የመከላከያ ክትባቶችና የሚሰጥበት የእንስሳት ዓይነት- ....... 46
አባሪ-4፡ የባለስልጣን መ/ቤቱ አሰራር ሥርዓት መግለጫ (System description/....... 48

## የክዋኔ ኦዲቱ ዋና ዋና ግኝቶችና ማሻሻያ ሃሳቦች ማጠቃለያ (Executive summary)

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ”ብሔራዊ የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት የእንስሳት ክትባት፣ ባዩሎጂካሎችና ሪኤጀንቶችን ማምረት፣ መድኃኒቶችን የማቀነባበር እና የአያያዝ ሥርዓት አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ ማከናወኑን ለማረጋገጥ በሥራው ዙሪያ የሚታዩ የአሠራር ክፍተቶችን እና የችግሮቹን መንስኤ በመለየት የማሻሻያ ሀሳቦችን በማቅረብ ተጠያቂነት እንዲጠናከር ለማድረግ ይህን የክዋኔ ኦዲት አካሂዷል፡፡

የክዋኔ ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian Performance Audit Standards) እና ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ሲሆን ዝርዝር ኦዲቱ የሸፈነው ከ2007 እስከ 2010 የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ድረስ ያሉ የሥራ ክንውኖችን ነው፡፡

በመሆኑም በክዋኔ ኦዲቱ የታዩ ዋና ዋና ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ምርቶቹን ወደ ሌሎች አህጉራት ተወዳድሮ ለመሸጥ የኢንስቲትዩቱ የአመራረት ቴክኖሎጂ ዓለም ዓቀፍ ገበያ የሚፈልገውን የመልካም አመራረት ዘዴን (Good manufacturing practice) ስታንዳርድ የማያሟላና የእውቅና ሠርተፊኬት የሌለው መሆኑ፣
- አማካይ በሆኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች የክትባት ማሰራጫ ጣቢያና ቀዝቃዛ መጋዘኖችን /Cold Room/ ባለመዘጋጀታቸው፡- በ-20$^{0}$C መቀመጥ ያለበት ክትባት በበረዶ ሣጥን ሲጓጓዝ መንገድ ላይ በረዶው እየቀለጠ ክትባቱ ለብልሽት እየተዳረገ እና ክትባቱ ለእንስሳቱ ሲሰጥ በሽታን የመከላከል ብቃቱ እየቀነሰ የመጣ መሆኑን፣
- የብሔራዊ የአደጋ ሥጋት ዝግጁነት ሥራ አመራር ኮሚሽን ቀደም ሲል በግብርና ሚኒስቴር ሥር በነበረበት ወቅት በተመረጡ የአገሪቱ አካባቢዎች ቀዝቃዛ መጋዘኖች /Cold Room/ አስገንብቶ ለተጠቃሚዎች ለማስተላለፍ እንዲቻል በኮሚሽኑ፣ በኢንስቲትዩቱ እና በኦሮሚያና ሶማሌ ክልሎች ግብርና ቢሮዎች ጋር በ2005 ዓ.ም የአጠቃቀም ሶስትዮሽ ውል ተፈራርሞ በዚሁ

መሰረት እንዲገነቡ ለሥራ ተቋራጭ ከተሰጡ 16 ቀዝቃዛ መጋዘኖች ውስጥ፡- የ7ቱ የካቲት 25/2002 ዓ.ም ተጀምሮ በ120 የሥራ ቀናት፣ የ7ቱ መጋቢት 27/2004 ዓ.ም ተጀምሮ በ90 የሥራ ቀናት እና የ2ቱ ሚያዝያ 12/2004 ተጀምሮ በ90 የሥራ ቀናት ለማጠናቀቅ ከሥራ ተቋራጭ ጋር ውል የተገባ ቢሆንም የ16ቱም ግንባታው ይጠናቀቃል ተብሎ ከታሰበው ከስድስት(6) ዓመት በላይ የዘገየ መሆኑ፣

- የተጀመሩት 13 ቀዝቃዛ መጋዘኖች በባለቤትነት የሚከታተላቸው አካል ባለመኖሩ ፀሀይ፣ ዝናብና ንፋስ እየተፈራረቀባቸው በመፈራረስ ላይ የሚገኙ መሆኑ፣ ለ16 ቀዝቃዛ መጋዘኖች 30% ቅድሚያ ክፍያ ለተቋራጮች የተከፈለው ሲሆን በኦሮሚያ ክልል በነጌሌ ቦረና፣ በደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልል ሚዛን አማን ከተማ እና በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሶሳ ከተማ ለመገንባት የታሰቡት ሶስት መጋዘኖች ግንባታቸው ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ያልተጀመረ መሆኑ፣
  - ኢንስቲቲዩቱ የደንበኞች ፍላጎት ያገናዘበ የክትባት ምርት በዓይነት፣ በመጠንና በጊዜ በማቅረብ የተጠቃሚዎችን ፍላጎት ማሟላት የሚገባው ቢሆንም የአፍታ (Foot and Mouth Disease)፣ የፍየሎች ሳንባ በሽታ የእብድ ውሻ፣ የግመል መከላከያ ክትባቶች እና የሳላይን ዉሃ በሚፈልጉት መጠንና ጊዜ የማይቀርብ መሆኑ፣ ኢንስቲቲዩቱ የሚያቀርበው አባሰንጋ (Anthrax) ባለ 100 ዶዝ፣ የአባጎረባ (Black leg) እና የጎሮረሳ (Bovine Pasteuellosis) የክትባት ምርቶች በባለ 50 ዶዝ ብቻ በመሆኑ የደንበኞች ፍላጎት እና አቅምን ያገናዘበ በተለያየ መጠን ተከፋፍሎ የማይቀርብ መሆኑ፣
- ኢንስቲትዩቱ ጥቅም ላይ ያልዋሉና ጊዜ ያለፈባቸው የክትባት ምርቶች አያያዝ፣ አጠቃቀምና የአወጋገድ መመሪያ ያላዘጋጀ መሆኑ፣ በየወረዳው ጥቅም ላይ ያልዋሉና ጊዜ ያለፈባቸዉ የክትባት ምርቶች ሳይወገዱ ለዓመታት ተጠራቅመው የሚገኙ መሆኑ፣ በአንዳንድ ወረዳዎች ክትባትን የንብረት አወጋገድ መመሪያን ተጠቅመው እንደማንኛውም አካባቢ የማይጎዳ ንብረት በመቁጠር የሚያስወግዱ መሆኑ፣ በኢንስቲትዩቱ ክትባት ማምረቻ ክፍል ውስጥ ካልሽም ክሎራይድ እና የተለያዩ ባይሎጅካሎች ከ15 ዓመት በላይ የተቀመጡ መሆኑ፣ እንዲሁም በኢንስቲትዩቱ የተበላሹ ኬሚካሎች ማጠራቀሚያ

መጋዘን/ስቶር ውስጥ ለብዙ ዓመታት ቤቱ አብሮ እስኪዝግ ድረስ የተቀመጡ ኬሚካሎች ያሉ መሆኑን፣

- በየክትባት ማምረቻ ክፍሎች ለክትባት ብክለት መከላከያ ለጤና ጠንቅ የሆኑትን ጨረር የሚጠቀሙ ሲሆን የጨረር መጠን በሰው ጤና ላይ ጉዳት የማያደርስ መሆኑን በሚመለከታቸው አካል እንዲረጋገጥ ያላደረጉ መሆኑና በትክክለኛው መንገድ ለመከላከል አስቸጋሪ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

በመሆኑም

- ኢንስቲትዩቱ ለአገሪቱ ብቸኛ የክትባት አምራች ተቋም በመሆኑ የክትባት ማምረቻ ክፍሎች በመልካም አመራረት ዘዴን (GMP) በማደራጀት፣ እና በምርት ሂደትና ከተመረተ በኃላ የሚከሰቱ ብክለትና ብክነትን በመቀነስ የሃገሪቱን ፍላጎት ከማሟሟላት አልፎ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ሆኖ ወደ ውጭ ሀገር የሚላከውን የክትባት መጠን በማስፋት ለሃገሪቱ ተጨማሪ የውጭ ምንዛሬ ለማስገኘት የበኩሉን አስተዋጽኦ ሊያደረግ ይገባል፡፡
- ኢንስቲትዩቱ አማካይ በሆኑ የአገሪቱ አካባቢዎች የራሱ የሆነ የክትባት ማሰራጫ ጣቢያዎችን በማዘጋጀት የሚያመርታቸው ክትባቶች ለተጠቃሚው ሕብረተሰብ በቀላሉ የሚደርስበትን ሁኔታ ሊያመቻችና በማጓጓዝ የሚከሰተውን ብክነት ሊቀነስ ይገባል፡፡
- ቀደም ሲል አሁን ብሔራዊ የአደጋ ሥጋት ዝግጁነትና ሥራ አመራር ኮሚሽን የተባለው በግብርና ሚኒስቴር ሥር በነበረበት ወቅት በተመረጡ የአገሪቱ አካባቢዎች ቀዝቃዛ መጋዘኖች /Cold Room/ አስገንብቶ ለተጠቃሚዎች ለማስተላለፍ ተብለው የተጀመሩትና ቅድሚያ ክፍያ የተከፈለባቸው 13 ቀዝቃዛ መጋዘኖች ግንባታቸው ተጀምሮ በአሁኑ ወቅት እየፈራረሱ ያሉና የሶስት ቀዝቃዛ መጋዘኖች ግንባታ ያልተጀመረ በመሆኑ ከሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል አስፈጻሚ አካላት ጋር በመሆን ያልተጀመሩትም ሆነ በጅምር ላይ ያሉት ተጠናቀው ወደ ሥራ የሚገቡበትን ሁኔታ በማመቻቸት ወደ ሥራ እንዲገቡ በማድረግ ለታለመላቸውት ዓላማ እንዲውሉ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ይህንንም በማድረግ ኢንስቲትዩቱ እያመረተ ለእንስሳት በሽታ መከላከያነት የሚቀርባቸው የክትባት ምርቶች በተለያየ አካባቢ በማጓጓዝ፣ በአከመቻቸትና አጠቃቀም ጉድለት ምክንያት በእንስሳት ላይ ጉዳት እያደረሰ

በህብረተሰቡ ዘንድ ቅሬታ የፈጠረበትን ምክንያት በጥናትና ምርምር በመፈተሽ የህብረተሰቡ ችግር ሊፈታ ይገባል፡፡

- ለአገሪቱም ሆነ ለኢንስቲትዩቱ ትልቁ ሀብት የሰው ኃይል በመሆኑ በየክትባት ማምረቻ ክፍሎች ለብክለት መከላከያ የሚጠቀሙት ጨረር መጠን ምን ያህል እንደሆነ ሥልጣን በተሰጠው አካል እንዲረጋገጥ በማድረግ ሠራተኞቹን ከአደጋ የሚከላከልበትን ሁኔታ ሊያመቻች ይገባል፡፡ በተጨማሪም በክትባት ማምረቻ ክፍሎች ውስጥ የሚከሰተውን ከፍተኛ ሙቀት በሠራተኞች ጤና ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ስለሚያሳድር ይህን ለማስወገድ የሚያስችል አፋጣኝ የመፍትሔ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡
- ኢንስትትቲዩቱ በአገሪቱ ወስጥ ያሉትን የእንስሳት በሽታ በጥናት በመለየት የደንበኞች ፍላጎት ያገናዘበ የመከላከያ ክትባት ምርት በዓይነት፣ በመጠን፣ በጊዜ እና በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ የበሽታ ስርጭት እንዲቀንስ በማድረግ የእንስሳት ሀብት ለአገሪቱ የግብርና ኢኮኖሚ የበኩሉን አስተዋጽኦ ኢንዲያበረክት ሊያደርግ ይገባል፡፡ እንዲሁም የእብድ ውሻ በሽታ ከሰው ጤና አንፃር፣ የአፍታ እና የአባጎረባ (Black Leg) ክትባቶች ዋጋቸው የህብረተሰቡን አቅም ያገናዘበ እንዲሆን ለማድረግ ለእንስሳትና ዓሳ ሀብት ሚኒስቴር አማራጭ መፍትሔዎችና አጥንቶ ሊያቀርብ ይገባል፡፡
- ኢንስቲትዩቱ የክትባት አያያዝና አወጋገድ መመሪያ በማዘጋጀትና ለተጠቃሚው ደንበኞች በማሰራጨት በየክልሉ፣ በየዞንና ወረዳ ተበላሽተው የተቀመጡ የክትባት ምርቶች እንዲወገዱ ሊያደርግና ወደፊትም ክትባቶቹ ሳይበላሹ ሥራ ላይ የሚውሉበትን መንገድ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር መፍትሔ ሊያስቀምጥ ይገባል፡፡
- ለአገሪቱም ሆነ ለኢንስቲትዩቱ ትልቁ ሀብት የሰው ኃይል በመሆኑ በየማምረቻ ክፍሎቹ ለብክለት መከላከያ የሚጠቀሙት ጨረር መጠን ምን ያህል እንደሆነ ሥልጣን በተሰጠው አካል እንዲረጋገጥ በማድረግ ሠራተኞቹን ከአደጋ የሚከላከልበትን ሁኔታ ሊያመቻች ይገባል፡፡

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. ብሔራዊ የእንስሳት ጤና ጥበቃ ኢንስቲትዩት በምርምር የታገዘ የተለያየ የእንስሳት ክትባት ምርቶችን እንዲያመርት በቀድሞው የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ሥር በ1956 ዓ.ም በደብረዘይት ተቋቋመ፡፡

2. ኢንስቲትዩቱ የክትባት ምርቶችን ለሀገር ውስጥም ሆነ ለውጭ ገበያ እያቀረበ በራሱ ገቢ መተዳደር እንዲችል ከ1991 ዓ.ም ጀምሮ በአዋጅ ቁጥር 25/84 እና በሚኒስቴሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 52/1991 የመንግስት የልማት ድርጅት ሆኖ የተቋቋመና በቦርድ የሚተዳደር ነው፡፡

3. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የመንግስት አስፈፃሚ አካላትን አደረጃጀት እንደገና ለማሻሻል ባወጣው አዋጅ ቁጥር 380/1996 መሠረት ብሔራዊ የእንስሳት ጤና ጥበቃ ኢንስቲትዩት ለግብርና ልማቱ ቀጥተኛ አጋዥ ኃይል በመሆኑ ከ1997 በጀት ዓመት ጀምሮ ተጠሪነቱ ለግብርና ገጠር ልማት ሚኒስቴር እንዲሆን ተደርጎ የነበረ ቢሆንም የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የመንግስት አስፈፃሚ አካላትን ስልጣን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/ 2008 ብሔራዊ የእንስሳት ጤና ጥበቃ ኢንስቲትዩት በቦርድ የሚተዳደር ሆኖ ተጠሪነቱ ለእንስሳትና ዓሣ ሀብት ልማት ሚኒስቴር እንዲሆን ተደርጎ ተቋቁሟል፡፡

4. ኢንስቲትዩቱ ክትባት የማምረት አቅሙን ከጊዜ ወደ ጊዜ በማጎልበት የእንስሳት ክትባቶችን በብዛትና በጥራት በማምረትና በማሰራጨት የሀገሪቱ ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት ለሆነው ግብርና የበኩሉን አስተዋፅኦ በማበርከት ላይ ሲሆን፣ ከዚህ በተጨማሪም ለሃገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ለማስገኘት ምርቶቹን ወደ ውጭ ሃገር በመላክ ላይ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም የዲያግኖስቲክ ኪት በማዘጋጀት ለተለያዩ የክልል ላቦራቶሪዎች በሽያጭ ያቀርባል፡፡ ኢንስቲትዩቱ የሚያመርታቸው ክትባቶች አይነት በአባሪ 4 ላይ ተያይዟል፡፡

5. ኢንስቲትዩቱ በሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 52/91 የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት ከ1994-1997 ዓ.ም የቢዝነስ ዕቅድ፣ ከ2003-2007 እና ከ2008–2012 የ5 ዓመት ስትራቴጅክ ዕቅድ በማውጣትና ከስትራቴጅክ ዕቅዱ የሚመነዘሩ የኢንስቲትዩቱ አቅም ያገናዘበና የገበያ ፍላጎትንም መሠረት ያደረገ በዓመታዊ ዕቅድ በመመራት እየተሻሻለ በመሄድ ላይ ያለ የመንግስት የልማት ድርጅት ነው፡፡

## የብሔራዊ እንሰሳት ጤና ጥበቃ ኢንስቲትዩት ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ አላማ

**የእንስቲትዩቱ ራዕይ**

6. ምርምር የተደገፈ ጥራት ያለው የእንስሳት በሽታ መከላከያ ክትባትና መድኃኒት በማምረት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪና ተመራጭ ሆኖ መገኘት፡

**የእንስቲትዩቱ ተልዕኮ**

7. በምርምር የተደገፉ ጥራትና ብቃት ያላቸው የእንስሳት በሽታ ክትባቶችና ባዮሎጂካሎች በማምረት እና መድኃኒቶችን በማቀነባበር ለእንስሳት አርቢው ሕብረተሰብ በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ የእንስሳት በሽታዎችን በመቆጣጠር እንዲሁም ክትባቶችን ወደ ተለያየ ውጭ ሃገር በመላክ የውጭ ምንዛሪ በማስገኘት ትርፋማነቱን አስጠብቆ መቀጠል፡፡

**የኢንስቲትዩቱ ዓላማ**

8. አለም ዓቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ጥራት ያለው የእንስሳት በሽታ መከላከያ ክትባት ምርት፣ የእንስሳት መድኃኒቶችን በዓይነት፣ በሚፈለገው መጠንና ጥራት አምርቶ በማቅረብ የሃገሪቱን የእንስሳት በሽታ ለመቆጣጠር ማስቻልና የእንስሳት አርቢው ህብረተሰብ ኑሮና ህይወቱ እንዲለወጥ ብሎም የሃገር ኢኮኖሚ እንዲያድግ የበኩሉን አስተዋፅዖ ማበርከት፣ ጥራት ያለው የእንስሳት በሽታ ምርመራ በማድረግ የእንስሳትና የእንስሳት ተዋፅዖ የውጭ ንግድ እንዲስፋፋ ማድረግና የክትባት ምርቶችን ወደ ውጭ ሃገር በመላክ የውጭ ምንዛሪ ማግኘት፡፡

## የብሔራዊ ጤና ጥበቃ እንስቲትዩቱ ስልጣንና ተግባር፡-

9. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 52/1991 አንቀፅ 5 መሠረት ኢንስቲትዩቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሎት ናቸው፡፡

- ✓ ለተለያዩ የእንስሳት በሽታዎች ዓለም ዓቀፍ ደረጃ ያላቸው የእንስሳት ክትባት ምርቶችን ማምረት፣
- ✓ ልዩ ልዩ የእንስሳት መድኃኒቶችን ማቀነባበር፣
- ✓ ለምርትና ለእንስሳት በሽታ ምርምር ሥራ የሚያገለግሉ ባዮሎጂካሎችና ሪኤጀንቶችን ማምረት፣
- ✓ ምርቶችን ለሃገር ውስጥና ለውጭ ገበያ አቅርቦ በመሸጥ ትርፋማነትን ማሳደግ፣

✓ በተጨማሪ ሌሎች ምርቶች ማምረት፣

ናቸው፡፡

## የኢንስቲትዩቱ ደርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል፡

### ድርጅታዊ መዋቅር

10. ብሔራዊ የእንስሳት ጤና ጥበቃ ኢንስቲትዩት በአዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀፅ 8 ንዕስ አንቀፅ "ለ"መሠረት ተጠሪነቱ ለእንስሳት እና ዓሣ ሃብት ልማት ሚኒስቴር ሆኖ በቦርድ የሚተዳደር ሲሆን በአንድ ዋና ሥራ አስኪያጅ የሚመራ ተቋም ነው፡፡ እንዲሁም ተጠሪነታቸው ለዋና ሥራ አስኪያጅ የሆኑ አስራ አንድ የሥራ ክፍሎች አሉት፡፡ እነዚህም (የውስጥ ኦዲት አገልግሎት፣ የህግ ባለሙያ፣ አይሲቲ አገልግሎት፣ የእቅድና በጀት ክፍል ፣ የለውጥ ሂደት ባለሙያ፣ የህዝብ ግንኙነት፣ የክትባት ማምረቻና ሽያጭ ዋና የሥራ ሂደት፣ የጥራት ቁጥጥር አገልግሎት፣ የጥናትና ምርምር ስርፀት የሥራ ሂደት፣ የግዥና ፋይናንስ አስተዳደር እና የሰው ሀብት አስተዳደር ሲሆን ድርጅታዊ መዋቅሩ **በአ**ባሪ 1 ተያይዟል፡፡

### የሰው ኃይል

11. ኢንስቲትዩቱ እንዲኖረው የተፈቀደለት የሰው ኃይል 280 ሲሆን በዚሁ መሰረት በህዳር ወር 2010 ዓ.ም በኢንስቲትዩቱ የነበረው የሰው ኃይል ወንድ 188 ሴት105 በጠቅላላ 293 ሰራተኞች ናቸው፡፡ የእነዚህ ሰራተኞች በትምህርት ደረጃ ሲተነተን ፒኤችዲ ወንድ 3 ሴት 0 ድምር 3 ፣ ማስተርስ ወንድ 18 ሴት 8 ድምር 26፣ ዲግሪ ወንድ 54 ሴት 20 ድምር 74፣ ዲፕሎማ ወንድ 30 ሴት 25 ድምር 55 12ኛና በታች ክፍሎች ወንድ 72 ሴት 50 ድምር 122 እና መፃፍና ማንበብ በሚችሉ ወንድ 11 ሴት 2 ድምር 13 ናቸው፡፡

## የፋይናንስ ምንጭ፡-

12. የብሔራዊ እንስሳት ጤና ጥበቃ የኢንስቲትዩቱ የፋይናንስ ምንጭ ተቋሙ ከሽያጭ የሚያገኘውን ገቢ ታሳቢ በማድረግ የየዓመቱን በጀት እቅድ በማዘጋጀት በቦርድ የሚፀድቅ መሆኑ ታውቋል፡፡ ኢንስቲትዩቱ በየአመቱ የሚገያኘውን ገቢ ሙሉ በሙሉ በበጀት እየያዘ የሚጠቀምበት እና ወደ መንግስት ካዝና ፈሰስ የማያደርግ ሲሆን ኢንስቲትዩቱ ከ2007 እስከ 2009 በጀት አመት ከሽያጭ ለማግኘት የቀደውን ገቢ እና የወጪ አፈጻጸም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

I. የኢንስቲትዩቱ የሀገር ውስጥና ወደ ውጭ ሀገር ልኮ በመሸጥ ለማግኘት የታቀደውና የተገኘው ገቢ አፈጻጸም

| ተ/ቁ | የሽያጩ ዓይነት | ተቋሙ ከሽያጭ ለማግኘት ያቀደው ገቢ | | | አፈጻጸም በብር | | | አፈጻጸም በመቶኛ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 2007 ዓ.ም | 2008 ዓ.ም | 2009 ዓ.ም | 2007 ዓ.ም | 2008 ዓ.ም | 2009ዓ.ም | 2007 | 2008 | 2009 |
| 1 | ከአገር ውስጥ | 98690000 | 109336550 | 125133700 | 79443631.17 | 108314537.70 | 123399513.6 | 80% | 99% | 99% |
| 2 | ከውጭ አገር | 17947500 | 17865000 | 29004000 | 12736092.17 | 20788678.22 | 28904624.30 | 71% | 116% | 100% |
| | **ድምር** | **116637500** | **127201550** | **154137700** | **92179723.67** | **129103216** | **152.304137.90** | **79%** | **101%** | **99%** |

II. የኢንስቲትዩቱ ላለፉት ሶስት አመታት የተመደበለት በጀትና በስራ ላይ የዋለው ወጪ

| ተ/ቁ | የበጀት ዓይነት | የተያዘ በጀት በብር | | | አፈጻጸም በብር | | | አፈጻጸም በመቶኛ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 2007 ዓ.ም | 2008 ዓ.ም | 2009 ዓ.ም | 2007 ዓ.ም | 2008 ዓ.ም | 2009እስከ ሰኔ 30 | 2007 | 2008 | 2009 |
| 1 | መደበኛ | 74754000 | 77,655,000 | 68,788,500 | 49,845,522.79 | 47,973,111.73 | 54,846,307 | 66.68% | 61.78% | 80% |
| 2 | ካፒታል | 42,345230 | 78,742,016 | 173,788,500 | 15,299723.19 | 38,168,598.98 | 140,868,062..4 | 36.13% | 48.47% | 81% |
| | **ድምር** | 117,099,230 | 156,397,016 | 242,577,000 . | 65,145,245.98 | 86,141,710.71 | 195734369 | 55.63% | 55.08% | 81% |

## የኦዲቱ ዓላማ፡-

13. የክዋኔ ኦዲቱ አላማ የኢንስቲትዩቱ የክትባት፣ ባዩሎጂካሎችና ሪኤጀንቶች የማምረት እና ልዩልዩ የእንስሳት መድኃኒቶችን የማቀነባበር ሥራ ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ ማከናወኑን ማረጋገጥ ሲሆን፤ ይህን በተመለከተ አሰራር ችግሮች ካሉ ለይቶ በማውጣት ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሀሳቦችን ለማቅረብ እና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡

## ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ

14. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ "ኢንስቲትዩት የእንስሳት ክትባት፣ ባዩሎጂካሎችና ሪኤጀንቶችን ማምረት፣ መድኃኒቶችን የማቀነባበር እና የአያያዝ ሥርዓት አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ ማከናወኑን መገምገም የሚል ነው፡፡

## የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) እና መመዘኛ መስፈርት

## የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ

15. ከላይ ለተለየው የኦዲት አካባቢ (Audit Area) ሶስት የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች /Audit Issues/ ተለይተዋል፡፡ እነርሱም ፡-

I. የእንስሳት ክትባት፣ ባዮሎጂካሎችና ሪኤጀንቶችን በማምረት እና መድኃኒቶችን የማቀነባበርና ተደራሽ የማድረጉ ሥራ ውጤታማ ስለመሆኑ መገምገም፣

II. የክትባት ማምረቻና የላብራቶሪ መሣሪያዎች፣ ሪኤጀንቶች፣ የክትባት ምርቶች አያያዝና አጠቃቀም ውጤታማ ስለመሆኑ መገምገም፣

III. ኢንስቲትዩቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በመሆን የክትባት ምርቶች ለተጠቃሚው የሚተዋወቁበትን እና ክትትልና ድጋፍ የሚደረግበትን የአሠራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያደረገ ስለመሆኑ መገምገም፡፡

የሚሉ ናቸው፡

## የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች

16. ከላይ የተመረጡትን ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ለመመዘን የሚያስችሉ 35 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅቷል፡፡ እነዚህን የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑት የኢንስቲትዩቱ መቋቋሚያ ደንብ 52/1991፣ የቢፒር የጥናት ሠነድ፣ የውጤት ተኮር ጥናት ሠነድ (BSC)፣ የማኔጅመንት ቃለ ጉባኤ፣ የኢንስቲትዩቱ ንብረት አስተዳደር መመሪያ፣ በኢንስቲትዩቱ ሠራተኛ ማህበር መካከል የተደረገ አራተኛ የኀብረት ስምምነት መመሪያ፣ National Veternary Institute product catalogue, በ2008 ዓ.ም በደንበኞች አገልግሎት የተዘጋጀ የእርካታ ዳሰሳ ጥናት ሪፖርት፣ የኢንስቲትዩቱ ስትራተጅክ ዕቅድ፣ የ(2003-2007)ና (2008-20112)፣ 2007.2008 እና 2009 ዕቅድና እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ናቸው፡፡ የተዘጋጁት የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ለኢንስቲትዩቱ ተልከው አስተያየት እንዲሰጥባቸው ተደርጓል፡፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶቹ **በአባሪ** 2 ተያይዟል፡፡

## የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

17. ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ ክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian performance Audit standards) እና ለመስሪያ ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ነው፡፡ ኦዲቱ የሸፈነው ከ2007 እስከ 2010 የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ድረስ ያሉ የሥራ ክንውኖችን ነው፡፡

18. ኦዲቱ በዋነኛነት የተከናወነው በብሔራዊ የእንስሳት ጤና ጥበቃ ኢንስቲትዩት ሲሆን በተጨማሪም በናሙና በተመረጡ አርብቶ አደር፣ ከፊል አርብቶ አደር፣ አርሶ አደሮች፣ እንስሳትን በማርባትና በማድለብ ተደራጅተው የሚንቀሳቀሱ ኢንተርፕራይዞችን እና የግል ባለሀብቶችንና ጉዳዩ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በአካል በመገኘት ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ እና ተያያዥ የሆኑ መረጃዎችን ጠይቆ በመከለስ ነው፡፡ በናሙና የታዩት ተቋማት ዝርዝር **በአባሪ** 3 ተያይዟል

## የኢንስቲትዩቱ የአሰራር ሥርዓት መግለጫ (Process description)

19. የብሔራዊ የእንስሳት ጤና ጥበቃ ኢንስቲትዩት የሥራ ሂደት መግለጫ **በአባሪ** 4 ተያይዟል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የኦዲት ግኝቶች

### የክትባቶች አመራረት ቴክኖሎጂ ቀልጣፋና ዉጤታማ መሆኑን በተመለከተ፡-

20. የኢኒስቲትዩቱ የክትባቶች አመራረት ቴክኖሎጂ ቀልጣፋ፣ ውጤታማና የሃገሪቱን ፍላጎት አሟልቶ ወደ ውጭ ሀገር በመላክ  የውጭ ምንዛሬ ለሃገሪቱ የሚያስገኝ ሊሆን ይገባል፡፡

21. በኦዲቱ ወቅት ኢንስቲትዩቱ ከሚያመርታቸው 22 የክትባት ዓይነቶች ውስጥ 13ቱን ወደ 26 አፍሪካ አገሮች የሚልክ መሆኑ ታውቋል፡፡ ይሁን እንጂ ምርቶቹን ወደ ሌሎች አህጉራት ተወዳደሮ ለመሸጥ የኢንስቲትዩቱ የአመራረት ቴክኖሎጂ ዓለም ዓቀፍ ገበያ የሚፈልገውን የመልካም አመራረት ዘዴ (Good manufacturing practice) (GMP) ስታንዳርድ የማያሟላና የእውቅና ሠርተፊኬት የሌለው በመሆኑ ተወዳድሮ ለመላክ እንዳልቻለ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎችና ለባለሙያዎቹ በቀረበ  መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

22. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የኢንስቲትዩቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው ፣

- እስከ አሁን ባለው የክትባት ማምረቻ ክፍሎቹ ሁሉም የመልካም አመራረት ዘዴን የማያሟሉ በመሆኑ አዲስ በተሰራው ህንጻ ላይ በተወሰኑ ክትባቶች ላይ ምርት ለመጀመር ዝግጅት ላይ መሆናቸውን የገለፁ መሆኑ፣
- በፊት ውስን ክትባቶች ብቻ  ይመረትባቸው የነበሩት ክፍሎች በአሁኑ ወቅት የበሽታ ስርጭትና የተጠቃሚዎች ፍላጎት እየጨመረ በመምጣቱ የምርት መጠኑ በመጨመሩና በአንድ ክፍል ውስጥ የተለያዩ ክትባቶች በመመረታቸው ቀደም ሲል በነበሩት ክፍሎች ላይ የቦታ  ጥበት መፍጠሩ፣
- የአፍታና የፍየል ሳንባ ክትባቶች የቴክኖሎጂ ሽግግር ውድ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ የማምረቻ መሣሪያዎችን ለማሻሻል ያልተቻለ መሆኑን፣
- የዶሮ ክትባቶችን በተመለከተ  ከማምረቻ ቦታ ጥበት ጋር ተያይዞ የሀገር ውስጥም ሆነ ከውጭ ሀገር ፍላጎት ጋር የተጣጣመ ምርት ማምረት ያልተቻለ መሆኑን፣
- የሬብስ ክትባት አዲስ የተጀመረ በመሆኑ በሙሉ አቅም ማምረት ስላልተጀመረ እጥረት የተከሰተ በመሆኑ ለወደፊቱ አቅርቦቱን የሚያሻሽሉ መሆኑን፣

በቃለ መጠይቅ እና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫና በሰጡት መላሽ ላይ ገልፀዋል፡፡

23. በተጨማሪም እ.ኤ.አ ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ የ ISO 9001:2008 የጥራት ማኔጅመንት ሲስተምን በመተግበር ከሚያመርቱት 22 ክትባቶች ውስጥ 13ቱን ወደ 26 አፍሪካ ሀገሮች የሚልኩ መሆኑን በኦዲት መውጫ ስብሰባ ወቅትና በረቂቅ ሪፖርት ላይ በጽሑፍ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

24. የክትባት ማምረቻ ክፍሎቹ የመልካም አመራረት ዘዴን (Good Manufacturing Practices) ሰርተፍኬት አለመኖሩ በዓለም ዓቀፍ ገበያ ተወዳድሮ አሸናፊ በመሆን ለሀገሪቱ የሚፈለገውን ያህል የውጭ ምንዛሪ እንዳይገኝ ሊያደርገው ይችላል፡፡ እንዲሁም የሚመረቱ ክትባቶች ለብክለትና ብክነት ከመዳረጉም በላይ የሚፈለገውን ያህል እንዳይመረት በማድረግ የሀገሪቱ እንስሳት ሀብት አስቀድሞ ከበሽታ ለመከላከል አዳጋች እንዲሆን ሊያደርገው ይችላል፡፡

## የክትባት ሽያጭ ጣቢያና ማቆያ መጋዘኖች /Cold Room/ ተዘጋጅቶ ክትባቶች ለተጠቃሚው ተደራሽ መሆናቸውን በተመለከተ፡-

25. ኢንስቲትዩቱ ክትባቶችን ለተጠቃሚው ህብረተሰብ ለማዳረስ እንዲችል በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የሽያጭ ቢሮዎችንና የክትባት ማቆያ መጋዘኖችን /Cold Room/ ከሚመለከተው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት አዘጋጅቶ አገልግሎት ላይ እንዲውል ሊያደረግ ይገባል፡፡

26. ይሁን እንጂ ኢንስቲትዩቱ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር አማካይ በሆኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች የክትባት ማሰራጫ ጣቢያና ቀዝቃዛ መጋዘኖችን /Cold Room/ ባለመዘጋጀታቸው፡-

- በ-20$^{0}$C መቀመጥ ያለበት ክትባት በበረዶ ሣጥን ሲጓጓዝ መንገድ ላይ በረዶው እየቀለጠ ክትባቱ ለብልሽት እየተዳረገ እና ክትባቱ ለእንስሳቱ ሲሰጥ በሽታን የመከላከል ብቃቱ እየቀነሰ የመጣ መሆኑን፣
- በክትባቱ መያዣ ላይ የተለጠፉት መግለጫዎች/ሌብሎች በረዶው ሲቀልጥ ስለሚያስለቅቃቸው የክትባቱ መጠን/ዶዝ ለመለየት ባለሙያዎች የሚቸገሩ መሆኑ፣
- በየወረዳ ክትባት መቆያ ቢሮዎች አካባቢ የተዘጋጀ ጄኔሬተር ባለመኖሩ መብራት ሲጠፋ ክትባቱ ለብልሽት የሚዳረግ በመሆኑ የክትባት ምርቶች ለእንስሳቱ ሳይሰጡ ለብልሽት የሚዳረጉ መሆኑን፣

በኦሮሚያ፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች፣ በአማራ እና በአፋር ክልሎች በናሙና ተመርጠው ከታዩት የዞኖችና የወረዳዎች የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ቢሮዎች/ ጽ/ቤቶች ባለሙያዎች ለቀረበላቸው መጠይቅ ከሰጡት ምላሽ ለማወቅ ተችሏል፡፡

27. በተጨማሪም የብሔራዊ የአደጋ ሥጋት ዝግጁነት ሥራ አመራር ኮሚሽን ቀደም ሲል በግብርና ሚኒስቴር ሥር በነበረበት ወቅት በተመረጡ የሀገሪቱ አካባቢዎች ቀዝቃዛ መጋዘኖች /Cold Room/ አስገንብቶ ለተጠቃሚዎች ለማስተላላፍ እንዲቻል በኮሚሽኑ፣ በኢንስቲትዩቱ እና በኦሮሚያና ሶማሌ ክልሎች ግብርና ቢሮዎች ጋር በ2005 ዓ.ም የአጠቃቀም ሶስትዮሽ ውል ተፈራርሞ ነበር፡፡ በዚሁ መሰረት እንዲገነቡ ለሥራ ተቋራጭ ከተሰጡ 16 ቀዝቃዛ መጋዘኖች ውስጥ፡-

- የ7ቱ የካቲት 25/2002 ዓ.ም ተጀምሮ በ120 የሥራ ቀናት፣ የ7ቱ መጋቢት 27/2004 ዓ.ም ተጀምሮ በ90 የሥራ ቀናት እና የ2ቱ ሚያዝያ 12/2004 ተጀምሮ በ90 የሥራ ቀናት ለማጠናቀቅ ከሥራ ተቋራጭ ጋር ውል የተገባ ቢሆንም የ16ቱም ግንባታው ይጠናቀቃል ተብሎ ከታሰበው ከስድስት (6) ዓመት በላይ የዘገየ መሆኑ፣
- በአሁኑ ወቅት በአፋር ክልል ሠመራ ከተማ፣ እና አብአላ፤ ሶማሌ ክልል ጅግጅጋ፣ ፊልቱ እና ሽንሌ፤ በኦሮሚያ ክልል ያቤሎ እና ሮቤ፤ በአማራ ክልል ኮምቦልቻ እና ሰሜን ጎንደር፤ በትግራይ ክልል ማይጨው እና ሽራሮ፤ በደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልል ጂንካ እና ጋምቤላ ክልል ጋምቤላ ከተሞች የተጀመሩት 13 ቀዝቃዛ መጋዘኖች በባለቤትነት የሚከታተላቸው አካል ባለመኖሩ ፀሀይ፣ ዝናብና ንፋስ እየተፈራረቀባቸው በመፈራረስ ላይ የሚገኙ መሆኑ፣
- የሥራ ተቋራጩ ጨረታ ላሸነፈባቸው 16 ቀዝቃዛ መጋዘኖች 30% ቅድሚያ ክፍያ የተከፈለው ሲሆን በኦሮሚያ ክልል በነጌሌ ቦረና፣ በደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልል ሚዛን-አማን ከተማ እና በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሶሳ ከተማ ለመገንባት የታሰቡት ሶስት መጋዘኖች ግንባታቸው ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ያልተጀመረ መሆኑ፣
- በአማራ ክልል ኮምቦልቻ ከተማ ቃሉ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት ግቢ ውስጥ የተገነባው ቀዝቃዛ መጋዘን ከተማ ውስጥ በሚገኘው የክልሉ የእንስሳት ጤና ምርምር ላብራቶሪ ግቢ ውስጥ መገንባት ሲገባው በቃሉ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት ግቢ በመገንባቱ እንዲሁም የደቡብ ክልል ጂንካ ከተማ የተገነባውና ሚዛን አማን እንዲገነባ ታቅዶ ያልተከናወነው የግንባታ ቦታዎች ክልሉም ሆነ ዞኑ በቦታው

ምርጫው ላይ ያልተሳተፉ በመሆኑ ባለሙያዎች ዘንድ ቅሬታ ያሳደረ መሆኑን፣

- ኢንስቲትዩቱ የቀዝቃዛ መጋዘኖቹ ግንባታ መቋረጡንና ለታለመለት ዓላማ አለመዋሉን ለሚመለከታቸው የመንግስት አካላት እንዲያውቁት ያደረገ ስለመሆኑ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑን፣

በኦሮሚያ፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች፣ በአማራ እና በአፋር ክልሎች በናሙና ተመርጠው ከታዩት ዞኖችና ወረዳዎች ለእንስሳትና ዓሣ ሀብት ባለሙያዎች ለቀረበላቸው መጠይቅ ከሰጡት ምላሽ ለማወቅ ተችሏል፡፡

28. ለ16 ቀዝቃዛ መጋዘኖች ግንባታ ከ 2002 እስከ 2005 ዓ.ም ብቻ ብር 11,417,315.80 እንዲሁም ከ2002 እስከ 2003 ዓ.ም ለዘጠኝ መጋዘኖች ኤሌክትሪክ ቆጣሪ ማስገቢያ ብር 671,884 ክፍያ የተፈፀመ ቢሆንም ከ9 ውስጥ ለ5ቱ መጋዘኖች የኤሌክትሪክ ቆጣሪ ያልገባላቸው መሆኑ፤ በአጠቃላይ በድምሩ ብር 12,089,199.80 ክፍያ ተፈፀሞ ሁሉም መጋዘኖች እስከ አሁን ሥራ ያልጀመሩ መሆኑን ለብሔራዊ የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ለቀረበ መጠይቅ ከተሰጠው ምላሽ፣ በሰነድ ክለሳና በመስክ ምልከታ በተደረገው ለመረዳት ተችሏል፡፡



*አፋር ክልል ሠመራ ከተማ ተጀምሮ በንፋስ ኃይል እየፈረሰ ያለ*



*በጂንካ ከተማ የተጀመረው ሣር እየበቀለበትና በመፍረስ ላይ ያለው*

29. ስለሁኔታው ጉዳዩ የሚመለከታቸው የኢንስቲትዩቱ የክትባት ማምረቻ፣ ሥርጭት እና ጥራት ቁጥጥር የሥራ ክፍል ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፡-

- ኢንስቲትዩቱ በሁሉም አካባቢ ቀዝቃዛ መጋዝን ማዘጋጀት ባይችልም የራሱ የሆነ በአራቱም የሀገሪቱ አቅጣጫዎች አዘጋጅቶ ወደ ተጠቃሚው መቅረብ አስፈላጊ መሆኑን ተቀብሎ ይህን ለማድረግ ግን የአቅም ውስንነት በመኖሩ ኢንስቲትዩቱ ብቻውን ማከናውን ስለማይችል ከመንግስትም ድጋፍ የሚጠይቅ መሆኑን፣
- የክትባት ሥርጭትን በተመለከተ የኢንስቲትዩቱ ኃላፊነት ባይሆንም ክትባቱ ለተጠቃሚ መድረስ ስላለበት ሙሉ በመሉ የሚሸፍን ባይሆንም ኢንስቲትትዩቱ ባለው ማቀዥቀዣ (በኮልድ ትራክ) ለተወሰኑ አካባቢዎች የማዳረስ ሥራ እየተከናወነ ቢሆንም የሥርጭቱ ችግር በኢንስቲትዩቱ ብቻ የሚፈታ ባለመሆኑ ከፌደራል እስከ ቀበሌ ደረስ ባለው የመንግስት አወቃቀር ሥርዓት ውስጥ ስለሚያልፍ ሁለም የድርሻቸውን ሊወጡ የሚገባ መሆኑን፤
- ተጀምሮ ያልተጠናቀቁና ርክክብ ያልተደረጉ ቀዝቃዛ መጋዘኖች የኢንስቲትዩቱ ባለሙያዎች ለእቅድ ዝግጅትና አቅድ አፈፃፀም ግምገማ ወደ መስክ በሄዱበት ወቅት በመጋዘኑ ዙሪያ የታዩትን ችግሮች በሪፖርት ለመንጅመንቱ ያቀረቡ መሆኑን፤

- ማኔጅመንቱም ለቦርዱ አቅርቦ እስከ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ድረስ እንዲደርስ የተደረገ መሆኑን፣

ገልጸዋል፡፡

30. በተጨማሪም የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት አስተያየት የተጠቀሱት ችግሮች የተከሰቱበት ምክንያት በቀድሞ ግብርና ሚኒስቴር ይሰራሉ ተብለው የተጀመሩት 16ቱ ቀዝቃዛ መጋዘኖች ተጠናቀው ሥራ ላይ እንዲውሉ ባለመደረጉ የተፈጠረ ክፍተት መሆኑን፤ ኢንስቲትዩቱ በቀዝቃዛ መጋዘን ላይ ያለው ኃላፊነት ተጠናቀው ርክክብ ከተፈፀመ በኃላ ቴክኒካል ድጋፍ መስጠት ብቻ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

31. ኃላፊዎቹ ከላይ የተገለጸውን መልስ የሰጡ ቢሆንም ተጀምረው ያልተጠናቀቁና ርክክብ ያልተደረገባቸው ስለ 13 ቀዝቃዛ መጋዘኖችን በተመለከተ ለሚመለከታችው የፌደራል እና የክልል አካላት የሶስትዮሽ ውል የተፈራረሙትን ጨምሮ እንዲያውቁት ባለመደረጉና በቦርድ በኩል ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲደርስ የተደረገ ስለመሆኑ የሚገልጽ ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል አልቻልንም፡፡

32. በመውጫ ስብሰባ ወቅት ለሚመለከታቸው የመንግስት አካላት እንዲያውቁት ያደረጉበትን ማስረጃ ሊያቀርቡ እንደሚችሉ የገለጹ ቢሆንም ከረቂቅ ሪፖርት ምላሽ ጋር አያይዘው ያቀረቡት ደብዳቤ የሚያስረዳው በኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል የተገነቡት የእንስሳት ማቀዝቀዣ ክፍሎችን በተመለከተ ከሚያዝያ 26-28/2008 ዓ.ም በጅግጂጋ ከተማ በተደረገው የዕትዕ2 የalignment መድረክ ላይ የተነሱትን ጥያቄዎችን መነሻ በማድረግ ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ መንግስት እንስሳትና ዓሣ ሀብት ሚኒስቴር ያሳወቀበትን ደብዳቤ እንጂ በሌሎች ክልሎች ውስጥ ስላሉት 13 የቀዝቃዛ መጋዘኖች ግንባታ መቋረጡንና ለታለመለት ዓላማ አለመዋሉን ያሳወቁበት ማስረጃ ያልቀረቡ በመሆኑ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል አልቻልንም፡፡

33. የክትባት ማቆያ ቀዝቃዛ መጋዘኖች ተዘጋጅተው ለተጠቃሚው እንዲቀርብ ባለመደረጉ ርቀት አካባቢ ያሉ ደንበኞች ክትባትን በሚፈለገው ጊዜ ለማግኘት ከመቸገራቸውም በላይ ከኢንስቲትዩቱ በበረዶ ሣጥን ተደርጎ ሲጓጉዙ በመንገድ ላይ በረዶ እየቀለጠ ክትባቱን ለብልሽት የሚዳርግ በመሆኑ፤ በክትባት መያዣ ላይ የሚለጠፉት የአጠቃቀም መግለጫዎች/ሌብሎች እየለቀቁ ክትባቱን ለመለየት የሚያስቸግር እና ወረዳዎች ከደረሰም በኋላ መብራት ሲጠፋ ክትባቱ ለብልሽት እየተዳረገ በመሆኑ በክትባቱ ውጤታማነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡

**የደንበኞች ፍላጎት ያገናዘበ የክትባት ምርት በዓይነት፣ በመጠንና በጊዜ ማቅረብን በተመለከተ፡-**

34. ኢንስቲትዩቱ የደንበኞች ፍላጎት ያገናዘበ የክትባት ምርት በዓይነት፣ በመጠንና በጊዜ በማቅረብ የተጠቃሚዎችን ፍላጎት ሊያሟላ ይገባል፡፡

35. ይሁን እንጂ፡-

የአፍታ (Foot and Mouth Disease, FMD) ፣ የፍየሎች ሳንባ በሽታ (Contagious caprine pleuropneumonia, CCPP) የእብድ ውሻ፣ የግመል ፈንጣጣ መከላከያ ክትባቶች እና የሳላይን ዉሃ በሚፈልጉት መጠንና ጊዜ የማይቀርብ መሆኑ፣

- ኢንስቲትዩቱ የሚያቀርበው አባሰንጋ (Anthrax) በባለ 100 ዶዝ፣ የአባጎርባ (Black leg) እና የጎሮርሳ (Bovine Pasteuellosis) የክትባት ምርቶች በባለ 50 ዶዝ ብቻ በመሆኑ የደንበኞች ፍላጎት እና አቅምን ያገናዘበ በተለያየ መጠን ተከፋፍሎ የማይቀርብ መሆኑ፣
- የአፍታ፣ የእብድ ውሻ፣ የፍያል ሳንባ እና የአባጎርባ (Black Leg) ክትባቶች ዋጋ ከፍተኛ በመሆኑ ህብረተሰቡ ክትባቶችን ገዝቶ ለመጠቀም ያለው ፍላጎት አነስተኛ እንዲሆን ያደረገ መሆኑን በናሙና ተመርጠው ከታዩት ከኦሮሚያ ክልል ለተመረጠ ዞንና በስሩ ከሚገኙ ወረዳዎች እንስሳት ሃኪም ባለሙያዎች መጠይቅ ቀርቦ ከሰጡት ምላሽ ለመረዳት የተቻለ መሆኑ፣
- በ2009 በጀት ዓመት የእብድ ውሻ/Rabies ክትባት በዶዝ 689,920፣ የአፍታ 500,000 ክትባት እና የሳለይን ውሃ በሊትር 225,200 ለማምርት ታቅዶ እንደቅደም ተከተላቸው 183,910 (27%)፣ 287200 (57%) እና 60,864 (27%) በማምረት ዝቅተኛ አፈፃፀም የተከናወነ መሆኑ፣

ከተከለሱት ሠነዶችና ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ለቀርበው ቃለ-መጠይቅ ከተሰጠው ምላሽ ለመረዳት ተችሏል፡፡

36. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የክትባት ማምረቻ፣ ሥርጭት እና ጥራት ቁጥጥር የሥራ ክፍል ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ የአፍታ፣ የእብድ ውሻ፣ የፍል ሳንባ መከላከያ ክትባቶች ከማምረቻ መሣሪያ ዘመናዊ አለመሆን ጋር ተያይዞ የፍላጎትን ያህል ማምረት አለመቻሉን፤ የግመል ክትባትን በተመለከተ አፋር ክልል ካሉት ክልሎች በግመል ሀብት ብዛት አንደኛ ቢሆንም በዚህ አካባቢ በህብረተሰቡ ዘንድ የግንዛቤ ማስጨበጫ የተፈለገውን ያህል ያልተሰራ ሲሆን፣ ምርቱ ግን በበቂ ሁኔታ እየተመረተ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

37. ስለሁኔታው የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ፡-

- የአፍታ (FMD) በእንስሳትና ዓሣ ሀብት ልማት ሚኒስቴር የቴክኖሎጂ ሽግግር ለማድረግ ፈንድ የማፈላለግ ሥራ እየተሰራ መሆኑን፣
- የፍየሎች ሳንባ በሽታ (CCPP) በፊት በዓመት ይመረት ከነበረው ከ 400,000 ዶዝ በአሁኑ ወቅት ከ5 ሚሊዮን ዶዝ በላይ ማምረት የተቻለ መሆኑን፤
- የሬብስ አዲስ መመረት የተጀመረ በመሆኑ ለማስፋፋት ጊዜ የሚጠይቅ መሆኑን፣
- በተለያየ የመያዣ መጠን ማድረጉ ዋጋን የሚያስጨምር በመሆኑ እንደሆነ፣
- የአፍታ፣ የእብድ ውሻ እና የአባጎርባ ከሌሎች ክትባቶች የማምረቻ ዋጋቸው ከፍተኛ በመሆኑ ሲሸጥ ዋጋው የሚጨምር መሆኑን፣
- የዕብድ ውሻ በሽታና የአፍታ ክትባቶች የምርት አፈፃፀም በ2009 ዓ.ም ዝቅ ያለበት ምክንያት መሥራት ያለባቸውን ያህል ባለመሥራታቸው የተፈጠረ ክፍተት መሆኑን እና የሣላን ውሃ በተመለከተ ግን በ2008 ዓ.ም በስቶር ውስጥ በመኖሩ ምክንያት በ2009 አፈፃፀሙ ዝቅ ያለ እንደሆነ፣

ገልፀዋል፡፡

38. ኢንስቲትዩቱ በእንስሳት ክትባት ምርት በአገሪቱ ውስጥ ብቸኛ አምራች ተቋም በመሆኑ ህብረተሰቡ አማራጭ የክትባት ምርት ማግኘት ስለማይችል የሀገሪቱ እንስሳት በተጠቀሱት በሽታዎች እንስሳት ለሞት ከማድረጉም በላይ ህብረተሰቡ ሊገዛው በሚችል መጠን ተመጥኖ አለመቅረቡ የተወሰኑ ክትባቶቹ እንዲባክኑ የሚያደርግ እና የህብረተሰቡ ኑሮ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡

**ለክትባት ማምረቻ የሚቀርበው ግብዓት መጠን፣ ጊዜና ጥራቱን የጠበቀ ስለመሆኑ በተመለከተ፡-**

39. ለክትባት ማምረቻ አገልግሎት የሚውሉ ግብዓቶች በሚፈለገው መጠን፣ ጥራትና ጊዜ የሚቀርብበት ቀልጣፋና ተጠያቂነት ያለው የአሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

40. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በኢንስቲትዩቱ ለክትባት ማምረቻ የሚቀርበው ግብዓት ቀደም ሲል ከተጠየቀው ስፔሲፊኬሽን ጋር ተገናዝቦ ገቢ የማይደረግ በመሆኑ፡-

- በአፍታ (Foot and Mouth Disease) ክትባት ማምረቻ ክፍል ለክትባት ማምረቻ ዲስፔንስንግ ማሽን 40ML እና 100ML ተጠይቆ 5ML በ25/06/08 ዓ.ም በEURO 5594.06 እና ሮሊንግ ማሽን 98 ኪ.ግ የሚመዝን መሣሪያ

ተጠይቆ 5 ኪ.ግ የሚመዝን በGBP (Great Britain pound) 1014.39 ተገዝቶ በ15/10/2009 ዓ.ም ገቢ የተደረገ መሆኑ፣

- ለክትባት ማምረቻ ከውጭ ሀገር የሚቀርቡ ግብዓቶች በወቅቱ ባለመቅረባቸው ክትባቶች የሚመረቱት በሚፈለገው ወቅት አለመሆኑ፣
- ከውጭ ሀገር ግዥ ተፈፅሞ ሊቭላቸውን በመቀየር ጥራት የሌለው ለክትባት ማምረቻ የሚሆን ግብዓት (ሴራም) ገቢ የተደረገ መሆኑ፣
- በሪኤጀንቶችና ንብረት ማከማቻ መጋዘን በ18/11/05 ዓ.ም 70.5 ኩንታል 7,938 USD ተገዝቶ ገቢ የተደረገ ALUMINIUM HYDROXID GEL የሚባል ኬሚካል እስከ አሁን አንድ ኩንታል ብቻ አገልግሎት ላይ የዋለ ሲሆን በአሁኑ ወቅት 69.5 ኩንታል በመጋዘን ውስጥ ያለ ሲሆን የመጠቀሚያ ጊዜዉ በታህሳስ 2011 ዓ.ም የሚያበቃ መሆኑ፤
- ኢንስትቲዩቱ 2009 ዓ.ም የGumbaro፤Fowl pox እና NCD Vaccine seed ዝግጅት ጥራትን ለማረጋገጥ ያቀደ ቢሆንም በዕቅዱ መሰረት ያላከናወነ መሆኑን፣

በየማምረቻ ክፍሎች በተደረገው ምልከታና ከተከለሱ ሠነዶች ለመረዳት ተችሏል፡፡

41. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የጥራት ቁጥጥርና ማረጋገጫ አገልግሎት የሥራ ክፍል ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ሮሊንግ ማሽንን በተመለከተ በወቅቱ ገቢ ሲደረግ ዕቃው ከተጠየቀው ጋር የማይገናኝ በመሆኑ እንዲቀየር ወይም ገንዘቡን ተመላሽ እንዲያደርግ ከአቅራቢው ጋር በድርድር ላይ መሆናቸውን፤ ሌሎች የተጠቀሱት ንብረቶች ከፍላጎት ጠያቂውና ከአቅራቢው ስህተት የተፈጠረ መሆኑን፤ በእቅድ አፈፃፀም ላይ የታየው ጉድለት የምርምር ሥራ ጊዜ የሚወስድ በመሆኑ በታቀደው መሠረት አለመከናወኑን ገልፀዋል፡፡

42. ስለሁኔታው የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ

- በ2009 በጀት ዓመት በውጭ ምንዛሪ እጥረት ምክንያት የማምረቻ ግብዓቶች ግዥን በ7 ወር በመዘግየቱ የተነሳ ምርቱ በወቅቱ ያልተመረተ መሆኑን፤
- የተጠየቀው 40 ML እና 100ML የማሽኑ ጡት ስላልተገኘ ለሙከራ 5ML እንዲመጣ በመደረጉ እንደሆነ፤

- ሮሊንግ ማሽን 98 ኪ.ግ የሚመዝን መሣሪያ ተጠይቆ 5 ኪ.ግ የሚመዝን ማምጣቱ የአቅራቢው ችግር በመሆኑ እንደገና ሌላ ፕሮፎርማ አቅርቦ እንዲወዳደርና እንዲያቀርብ ለማድረግ በሂደት ላይ መሆናቸውን እና
- ALUMINIUM HYDROXID GEL በፓኬጂንግ የፍላጎት መግለጫ ስህተት ተፈጥሮ ከፍላጎት በላይ እንዲመጣ የተደረገ በመሆኑ ሌሎች ተቋማት ኬሚካሉን የሚጠቀሙ ካሉ እንዲወስዱ እያፈላለጉ መሆናቸውን

ገልፀዋል፡፡

43. የኢንስቲትዩቱ የሥራ ኃላፊዎች ይህን ምላሽ ይስጡ እንጂ ሮሊንግ ማሽንን በተመለከተ ዕቃው እንዲቀየር ወይም ገንዘቡን ተመላሽ እንዲያደርግ ከአቅራቢው ጋር በድርድር ላይ መሆናቸውን እና ሌሎች የተጠቀሱት ንብረቶች ከፍላጎት ጠያቂውና ከአቅራቢው ስህተት የተፈጠረ መሆኑን የገለጹ ቢሆንም ዕቃው ስለመቀየሩ ወይም ገንዘቡ ተመላሽ ስለመደረጉ እንዲሁም በስህተት ከፍላጎት በላይ እንዲመጣ የተደረገው 69.5 ኩንታል ALUMINIUM HYDROXID GEL ለሌሎች ፍላጎት ላላቸው ተቋማት እንዲወስዱ እያፈላለጉ ስለመሆኑ የቀረቡ ማስረጃዎች ባለመኖራቸው የተሰጠውን መልስ መቀበል አልቻልንም፡፡

44. ኢንስቲትዩቱ በዘረጋው ሥርዓት መሰረት ለክትባት ማምረቻ አስፈላጊ የሆኑት ግብዓቶች ምን እንደሆኑ እና በምን ያህል መጠን መገዛት እንዳለባቸው የሚገልጽ ጥያቄ በቅድሚያ በሚመለከታቸው ባለሙያዎች ተዘጋጅቶ የግዥ ጥያቄ ባለመቅረቡ እና ተገዝተው ገቢ የተደረጉት የክትባት ማምረቻ ግብዓቶች በተጠየቀው የግዢ ጥያቄ መሰረት መሆናቸው ታይቶ በሚመለከተው ባለሙያ ጥራታቸው ተፈትሾና ተረጋግጦ ገቢ ያልተደረገ በመሆኑ ኢንስቲትዩቱ በሚያመርተው ምርት ውጤትና ትርፋማነት ላይ አሉታዊ ተፅኖ ያሳድራል፡፡

### ሪኤጀንቶችን የማምረትና መድኃኒቶችን የማቀነባበር ሥራ ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፡-

45. ኢንስትቲዩቱ ሪኤጀንቶችን በማምረት እና መድኃኒቶችን በማቀነባበር ለሪኤጀንትና ለመድኃኒት ግዥ የሚወጣ የውጭ ምንዛሬ ሊቀንስ ይገባል፡፡

46. ይሁን እንጂ ኢንስትቲዩቱ በተሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት መሠረት የእንስሳት መድኃኒት አቀነባብሮ ማቅረብ ባለመቻሉ፡-
    - በድንበር አካባቢ በህገወጥ መንገድ የእንስሳት መድኃኒት ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ አንዱ ምክንያት መሆኑ፣

- ክልሎች ከውጭ ሀገር ከሚያስገቡ ነጋዴዎች ገዝተው ለተጠቃሚው አርሶ አደር፣ አርብቶ አደር እና ከፊል አርብቶ አደር ስለሚያቀርቡ የመድኃኒቱ ዋጋ ተጠቃሚዎች ቅሬታ ያሳደረ መሆኑ፣
- ከውጭ ሀገር ተገዝተው የሚቀርቡ የእንስሳት መድኃኒቶች የመፈወስ አቅማቸዉ አርኪ አለመሆንና ብዙ አማራጭ መድኃኒቶቹን ለማግኘት ተጠቃሚዎች የተቸገሩ መሆኑ፤ ለምሳሌ Ant fungus፤ Diuretics፤ Anesthetic፤ Antiviral እና Supportive የተባሉ መድኃኒቶች በገበያ ላይ ማግኘት ባለመቻሉ በሽታው እንስሳቶችን እያጠቃ መሆኑን፣

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱት መረጃዎችና በመስክ ላይ ለእንስሳት ሀኪሞች ለቀረበላቸው መጠይቅ ከሰጡት መልስ ለመረዳት ተችሏል፡፡

47. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የክትባት ማምረቻ፣ ሥርጭት እና ጥራት ቁጥጥር ማረጋገጫ አገልግሎት የሥራ ክፍል ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ኢንስቲትዩቱ የተለያየ የእንስሳት መድኃኒቶችን የማቀነባበር ሥራ ለመጀመር ካቀደ ረዥም ጊዜ ቢሆንም በተለያዩ አሳማኝ ምክንያቶች ሊዘገይ የቻለ መሆኑን፤ ነገር ግን በአሁኑ ሰዓት የፋብርካው ሕንፃ ተጠናቆ የውስጥ ክፍፍልና የማሽን ተከላ ሥራው የተጀመረ በመሆኑ በቅርብ ጊዜ የሙከራ ምርት የሚጀምር መሆኑን ገልፀዋል፡፡

48. ስለሁኔታው የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራአስኪያጅ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ኢንስቲትዩቱ በአዋጅ የተሰጠው ኃላፊነት ቢሆንም በራሱ በጀት የሚተዳደር በመሆኑ አቅም እስኪገነባ ድረስ ሳይተገበር የቆየ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት የፋብሪካው ግንባታ እየተከናወነ በመሆኑ በቀጣይ ዓመት የተጠቀሱትን ክፍተቶች ለመሙላት ምርት ማምረት የሚጀምር መሆኑን በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ገፀዋል፡፡

49. የእንስሳት መድኃኒት የማቀነባበር ሥራ ተግባራዊ ባለመደረጉ ሀገሪቱ በየዓመቱ ለእንስሳት መድኃኒት ግዥ ወደ ውጭ የሚሄደውን ገንዘብ በአገር ውስጥ እንዳይቀር ከማድረጉም በላይ ከውጭ ሀገር ተገዝተው የሚቀርቡት መድኃኒቶች የመጠቀሚያ ጊዜያቸው የቀረበ፣ በየጊዜው ተመሳሳይነት ያለው መድኃኒት ብቻ የሚቀርብ በመሆኑ ከበሽታው ጋር በመላመድ መድሃኒቱ ለእንስሳቱ ሲሰጥ ፈዋሽ እንዳይሆን ሊያደርግ ይችላል፡፡

**የሚመረቱት የክትባት ምርቶች ጥራቱ፣ ደህንነቱና ፍቱንነቱን በተመለከተ፡-**

50. ኢንስቲትዩቱ የሀገሪቱን የእንስሳት ጤና ለማስጠበቅ ጥራቱ፣ ደህንነቱና ፍቱንነቱ የተረጋገጠ የእንስሳት ክትባት በማምረት ለተጠቃሚ አካላት ሊያቀርብ ይገባል፡፡

51. ይሁን እንጂ በኢንስቲትዩቱ ተመርተው የተሠራጩት አንዳንድ የክትባት ምርቶች በተለያየ አከባቢ ላይና ጊዜያት በሽታን የማይከላከል ከመሆኑም በላይ በእንስሳት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እያሳደረ መሆኑ፣ ለማሣያ፡-በኦሮሚያ ክልል፡-

- በምዕራብ አርሲ ዞን ኮኮሣ ወረዳ በ3,600 እንስሳት ላይ ጉዳት ያደረሰ መሆኑ፣
- 2007 ዓ.ም በምዕራብ አርሲ ዞን የጎሮርሳ ክትባት ባች ቁጥር 5/14 የአገልግሎት ጊዜ ማብቂያው 9/15 የሆነ 2009 ዓ.ም አርሲ ዞን ሴሩ ወረዳ የጎሮርሳ ክትባት ባች ቁጥር 6-16 በ10/5/09 እንስሳቱ ክትባቱን ከተከተቡ ከ 9፡00 ሰዓት በኋላ አንድ በሬና አንድ ጊደር ላይ ጉዳት ያደረሰ መሆኑ፣
- በ2009 ዓ.ም በሰሜን ሸዋ ዞን የአባ ጎርባ በሽታ መከላከያ ክትባት ባች ቁጥር-8 በ19/06/09 ለእንስሳቱ ክትባት ከተከተቡ በኋላ አራት እንስሳት (ሦስት በሬና አንድ ጊደር) ላይ ጉዳት ያደረሰ መሆኑ፣
- በ2007 ዓ.ም የሐረሪ ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የጉርብርብ በሽታ መከላከያ ክትባት 20,000 ዶዝ ከኢንስቲትዩቱ ወስዶ እንስሳቱ እንዲከተቡ ካደረገ በኋላ የበሽታ ስርጭቱ ከመጨመሩም በላይ የተወሰኑ እንስሳት ላይ ጉዳት ያደረሰ መሆኑ፣
- የላምፒስኪን ክትባት የመከላከል ብቃቱ ከ20% እስከ 30% ብቻ መሆኑን፣
- ኢንስቲትዩቱ የክትባት ጎንዮሽ ጉዳት ማፍረሻ ከክትባቱ ጋር አብሮ ለተጠቃሚ የማይቀርብ መሆኑ፣
- የክትባት ጎንዩሽ ጉዳት (የሚያሳየው ምልክቶች) በበራሪ ወረቀት (leaflet) ተዘጋጅቶ ከክትባቱ ጋር አብሮ ለተጠቃሚ የማይቀርብ መሆኑ፣

በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠ በታዩት በኦሮሚያ፣ በአማራ እና በደቡብ ብ/ብ/ሕ በመስክ ለእንስሳት ሃኪሞች ቃለመጠይቅ ቀርቦ ከተሰጡት ምላሾችና በኢንስቲትዩቱ ከተከለሱት መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

52. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የክትባት ማምረቻ፣ ሥርጭት እና ጥራት ቁጥጥርና ማረጋገጫ አገልግሎት የሥራ ክፍል ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ

- በተለያዩ አካባቢዎች ችግር ፈጠሩ የተባሉት ክትባቶች እራሱን ክትባት ወደ ኢንስቲትዩቱ በማምጣት በግቢ ውስጥ በሚገኙት እንስሳት ላይ

ከተቀመጠለት መጠን በላይ በመከተብ ሲሞከር በእንስሳቱ ላይ ምንም ዓይነት ጉዳት ያላደረሰ መሆኑን፤ ምናልባት ጉዳት ደረሰባቸው የተባሉት እንስሳት በውስጣቸው የራሳቸው የሆነ ችግር ያለባቸው ሊሆኑ እንደሚችሉ ፤

- ከኢንስቲትዩቱ ተመርተው የሚወጡ ክትባቶች ጥራታቸው ተረጋግጠ የሚወጣ ቢሆንም ከተሰራጨ በኋላ በተለያየ ምክንያቶች ውጤታማ የማይሆንበት ሁኔታዎች እንደሚኖሩ፣ ለምሳሌ፡-የታመሙና ያልተመሙ እንስሳትን ለይቶ የማስከተብ ችግር፣ ክትባቱ ሲሰጥ የባለሙያ የአሰጣጥ ችግር፣ እራሱ የክትባቱ ባህርይ ጋር የተያያዘ ችግር፣ የክትባቱ አያያዝ፣ አቀማመጥ እና ክትባቱ ስሰጥ የሚጠቀሙበት ስሪንጅ ንፅህና ችግር በመኖሩ ክትባቱ በሽታ ላይከላከል ስለሚችል የካሳ ክፍያ ለመፈፀም እንስሳት ላይ ጉዳት ያደረሰበትን ምክንያቶች መንስኤ በጥናት ተለየቶ ያልተረጋገጠ በመሆኑ

ሥርዓቱን ዘርግቶ ተግባራዊ ለማድረግ አስቸጋሪ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

53. ስለሁኔታው የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ፡-

- ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ተደርጎ ከክትባቱ በህርይ ጋር በተያያዘ ችግሩ በሚታይባቸው እንስሳት የማርከሻ መድኃኒት መውጋት እንደሚያስፈልግ ስምምነት ላይ የደረሱ መሆኑን፤
- በተካሄደው የባለድርሻ አካላት መድረክ ላይ ዘላቂ መፍትሔ እስኪገኝ የአከታተብ መመሪያ ወጥቶ ለክልሎች እንዲሰራጭ የተደረገ መሆኑን፣
- የክትባት ጎንዮሽ ጉዳት መፍረሻ ከክትባቱ ጋር አብሮ መቅረብ ያለባቸው ክልሎች መሆኑን ከክልሎች ጋር በተደረገው መደረክ ኃላፊነት የተሰጣቸው መሆኑን፣
- በበራሪ ወረቀት ላይ የጎንዮሽ ጉዳት አስመልክቶ መወሰድ ያለበት እርምጃ በፊት የማይጠቀስ ቢሆንም ተካቶ እንዲዘጋጅ የተደረገ መሆኑን፣

ገልፀዋል፡፡

54. የኢንስቲትዩቱ የሥራ ኃላፊዎች ይህንን ምላሽ ይስጡ እንጂ በኦዲቱ ወቅት የቀረበው ያልተፈረመ የ2007 ዓ.ም የደንበኞች ቀን የምክክር መድረክ ላይ የተያዘ ቃለጉባኤ ከመሆኑም በላይ የክትባት ጎንዮሽ ጉዳት ማፍረሻ የማቅረብ ኃላፊነት የክልሎች ስለመሆኑ የተገለጸ ሀሳብ እንጂ ክልሎች ኃላፊነቱን ወስደው የክትባት

ጎንዮሽ ጉዳት ማፍረሻ የማቅረብ ኃላፊነት የተሰጣቸው ስለመሆኑ የሚገልጹ ማስረጃዎች ባለመቅረባቸው እንዲሁም እንስሳት ላይ ጉዳት የደረሰበትን ምክንያት/መንስኤ በጥናት ማረጋገጥ ያለበት አካል ያልተለየ በመሆኑ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል አልተቻለም፡፡

55. በኢንስቲትዩቱ ተመርተው የሚያሰራጩ የእንስሳት በሽታ መከላከያ ክትባቶች በእንስሳት ላይ የሚያመጡትን አዎንታዊና አሉታዊ ተፅዕኖ በየጊዜው ምርምርና ጥናት በማድረግ ክትባቶቹን በማሻሻል ለተጠቃሚው ምላሽ ካልተሰጠ ህብረተሰቡ እንስሳትን ከማስከተብ እየራቀ፣ በሽታው ደግሞ እየተስፋፋ በመሄድ በአርሶ አደሩ፣ በአርብቶ አደሩ እና በከፊል አርብቶ አደሩ ኑሮ ላይ ተፅዕኖ ከማሳደሩም በላይ የእንስሳት ሀብት ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ የበኩሉን ሚና እንደይጫወት ሊያደርግ ይችላል፡፡

## ኢንስቲትዩቱ በክትባት አያያዝና አጠቃቀም ዙሪያ ለተጠቃሚዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ማከናወኑን በተመለከተ፡-

56. እንስትቲዩቱ በእንስሳት ጤና አጠባበቅ ረገድ ከባለድርሻ አካላት ጋር የጋራ ትብብርና የልምድ ልውውጥ መድረክ በማዘጋጀት የክትባት አያያዝ እና አጠቃቀምን በተመለከተ ለተጠቃሚው የግንዛቤ ማሰጨበጫ ሥራና የዕውቀት ሽግግር የሚያደረግበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

57. ይሁን ኢንጂ በኦዲቱ ወቅት፤-


- ኢንስቲትዩቱ እያመረተ የሚያሰራጫቸዉ የክትባት ምርቶች በትክክል በተቀመጠዉ የአጠቃቀም መመሪያ መሰረት ጥቅም ላይ መዋሉን ክትትል እና ቁጥጥር የሚያደርግበት ሥርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፤
- በ+4$^0$c መቀመጥ ያለባቸው የክትባት ምርቶች በማዳበሪያ ከረጢት ተቋጥረው የፀሐይ ብርሃን በሚገባበት ክፍል ውስጥ የተቀመጡ መሆኑ፣
- በክትባት ማስቀመጫ ክፍል ውስጥ የተለያዩ ዕቃዎች፣ የመጠቀሚያ ጊዜ አልፎባቸው የተበላሹ ክትባቶችና መድኃኒቶች እና ጤነኛ /አገልግሎት ላይ ከሚውሉ ክትባቶችና መድኃኒቶች ተለይተው ያልተቀመጡ መሆኑ፣
- የዶሮ ክትባት አሰጣጥ ላይ በባለሙያዎች ዘንድ የግንዛቤ እጥረት የፈጠረ መሆኑ፣
- ክትባቶችን በንብረት አያያዝና አወጋገድ መመሪያ መሠረት የሚያስወግዱ ወረዳዎች መኖራቸው፣

- ነባር ክትባቶች ስለመሻሻላቸውና አዳዲስ ክትባቶች ስለመፈጠራቸዉ ተጠቃሚው እንዲያውቅ ያልተደረገ መሆኑ፣
- ክትባቶች በበረዶ ሣጥን ሲጓጓዙ በመያዣው ላይ የሚለጠፉት ሌብሎች ስለሚለቁ በመልክና በመያዣ የሚመሳሰሉት ክትባቶችን ለይቶ ለእንስሳት ለመስጠት ባለሙያዎች የሚቸግሩ መሆኑ፣
- ተጠቃሚው ኢንስቲትዩቱ የሚያመርታቸው ክትባቶች በዓይነት በሙሉ ለይቶ የማያውቁ መሆኑ፣
- ከዩኒቨርስቲ ተመርቀው በእንስሳት ጤና ባለሙያ ሆነው በየወረዳው የተመደቡት የእንስሳት ሃኪሞች በትምህርት ቤት የቀሰሙትን ዕውቀት በተግባር ለመተርጎም የሚቸገሩ መሆኑ፣
- አንዳንድ የእንስሳት አርቢዎች በ-20$^0$C እና በ+4$^0$C በሆነ የቅዝቃዜ መጠን መቀመጥ ያለባቸውን የክትባት ምርቶች በኪሳቸዉ ይዘዉ የሚንቀሳቀሱ መሆኑ፣
- ስለክትባት ግንዛቤ የሚፈጥሩ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት በሬድዬ/ቴሌቪዥን በተለያየ ቋንቋ ለማስተዋወቅ በ2007፣ 2008፣ 2009 በጀት ዓመት የታቀደ ቢሆንም የማስተዋወቅ ስራው ያልተሰራ መሆኑን፣

በመስክ ምልከታ፣ በሰነድ ክለሳና ለባለሙያዎች መጠይቅ ቀርቦ ከተሰጡት ምላሾች ለመረዳት ተችሏል፡፡ በነጌሌ ቦረና ጉጅ ዞን በወረዳ የክትበት አያያዝን በተመለከተ ማሣያ ፎቶዎች



በነጌሌ ቦረና ጉጂ ዞን ቦሬ ወረዳ በ+4$^0$c መቀመጥ ያለባቸው ክትባቶች ከተለያዩ ንብረቶች ጋር ተደባልቆ የተቀመጡ መሆኑን የሚያሣይ



ነጌሌ ቦረና ጎጂ ዞን ሊበን ወረዳ በፍሪጅ ውስጥ መቀመጥ ያለባቸው የክትባት ምርቶች በማዳበሪያ ከረጢት መሬት ላይ የቀመጠ መሆኑን የሚያሣይ



በኮምቦልቻ ከተማ ቃሉ ወረዳ መብራት በመጥፋቱ በረዶው በፍሪጅ ውስጥ ቀልጦ የክትባቱን ሌብል እያስለቀቀ ስለመሆኑ የሚያሳይ



በጉጂ ዞን አዶላ ወዩ ወረዳ ክትባቶች በካርቶን ተደርገው ከተለያዩ የተበላሹ ንብረቶች ጋር አንድነት የተቀመጡ መሆኑን የሚያሣይ

58. ስለጉዳዩ የክትባት ማምረቻና ሥርጭት የሥራ ክፍል ኃላፊዎች እና የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራአስኪጅ ተጠይቀው በሰጡት መልስ እና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት የተጠቀሱት ችግሮች ትክክለኛ መሆናቸውን፣

- ችግሮቹ የተከሰቱበት ምክንያት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ባለመሰራቱ ብቻ ሳይሆን በመንግስት መሥሪያ ቤቶች አወቃቀር ሥርዓት ከፌዴራል እንስሳትና ዓሣ ሀብት ልማት ሚኒስቴር እስከ ቀበሌ ድረስ ያሉት ባለሙያዎች ኃላፊነታቸውን በትክክል ባለመወጣታቸው እንደሆነ፣
- አቅም የፈቀደላቸውን ሁሉ በዞን፣ በወረዳ እና በቀበሌ ላይ ካሉት ባለሙያዎች ጋር በቀጥታ በመገናኘት እየሠሩ መሆናቸውን፣
- የክትባትን ቅዝቃዜ ሰንሰለትን አስመልክቶ ስለሚሰጡ ሥልጠናዎች ማንዋል ተዘጋጅቶ ለደንበኞች አገልግሎት ባለሙያ የተሰጠና ይሄው ማንዋል ለመድኃኒትና መኖ ቁጥጥር ጋይድላይን ውስጥ እንዲገባ የተደረገ መሆኑን፣
- ሥራው እየተሠራ ያለ ቢሆንም ከተደራሽነት አንፃር ክፍተት ያለበት መሆኑን፣
- የክትባቱ ሌብሎች የማይለቅ ለማድረግ ብዙ ጥረት የተደረገና መሻሻሎችም ያሉ ቢሆንም ለወደፊቱም በደንብ ለማሻሻል ገበያ እያፈላለጉ መሆናቸውን፣
- ኢንስቲትዩቱ ከ2008 ዓ.ም በስተቀር በየዓመቱ የደንበኞች ቀን ላይ ከዶሮ ፋርም /እርሻ/ ባለቤቶች ጋር እቅድ አዘጋጅቶ የልምድ ልውውጥና የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ያከናወኑ መሆኑን፣
- ከክልሎች ጋር በዓመት አንድ ጊዜ በዕቅድ ግምገማ ወቅት አጀንዳ በማዘጋጀት የሚነሱ ችግሮች በማሰባሰብ ውይይት የሚያደርጉ ቢሆንም ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ግን በክትባቱ ዙሪያ በቅንጅት የግንዘቤ ማስጨበጫ ሥራ ያለመስራት ክፍተት በመኖሩ ለወደፊቱ ትኩረት ሰጥተው እንደሚሰሩ

ገልጸዋል፡፡

59. በሚዲያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራን በተመለከተም በ2007 ዓ.ም ቅዳሜ ማታ ከ3፡00 በኋላ በኢትዮጵያ ራዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ሁልጊዜ በአማርኛ ቋንቋ ብቻ የማስተዋወቅ ሥራ የተሰራ ቢሆንም በ2008 እና 2009 በጀት ዓመት በተለያዩ ምክንያቶች ያልተሠራ ሲሆን አሁን በ2010 በጀት ዓመት በእሁድ መዝናኛ ፕሮግራም በኢቢሲ1 የአንድ ዓመት ብር 88,920 ክፍያ ተፈፅሞ እንዲተላለፍ

እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ለአብዛኛው አርብቶ አድርና አርሶ አደር ተደራሽ ሆነው በሬዲዮ የግንዛቤ ማስጨበጫ ለምን እንዳልተሰራ ምላሽ በላይ አልሰጡም፡፡

60. ስለክትባቱ ተከታታይነት ባለው መልኩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በመሆን የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ባለመሠራቱ ክትባቶቹ መቀመጥ ባለባቸው የቅዝቃዜ መጠን እየተቀመጡ ባለመሆኑ ለታለመላቸው ዓላማ ሳይውሉ ለብልሽት የሚዳረጉ በመሆኑ በክትባቱ የመከላከል ብቃት ላይ ህብረተሰቡ ቅሬታ እንዲኖረው ከማድረጉም በላይ ኢንስቲትዩቱ የተቋቋመበትን ዓላማ እንዳያሳካ ሊያደርገው ይችላል፡፡ በተጨማሪም የማስተዋወቅ ሥራው ተከታታይነት ባለው ሁኔታና ለተጠቃሚው ተደራሽ በሆኑ በተለያዩ የመገናኛ ብዙኃን እና በክልል ቋንቋዎች ባለመሰራቱ ተጠቃሚ የሆኑ ደንበኞች በኢንስቲትዩቱ የሚመረቱትን የክትባት ዓይነቶችና አጠቃቀም በሙሉ ለይተው እንዳያውቁ አድርጓል፡፡

## የክትባት ምርት እድገት ማፋጠንን፣ ማስፋፋትንና ማሻሻልን በተመለከተ፡-

61. የክትባት ምርት እድገት ለማፋጠንና ለማስፋፋት ጥናትና ምርምር በማድረግ ነባር ክትባቶች ሊሻሻሉና አዳዲስ ክትባቶች ደግሞ ሊፈጠሩ ይገባል፡፡

62. ይሁን እንጂ በኢንስቲትዩቱ፡-

- በጥናት የተደገፉ አዳዲስ ክትባቶችን የማውጣትና ነባር ክትባቶችን የማሻሻል ሂደት አዝጋሚ መሆኑ፣
- የእንስሳት MCF (Malignant Cateral Fiber፣ የግመል Unknown Camel Disease እና Respiratory Disease Complex) የተባሉ በሽታዎች በኢንስቲትዩቱ ክትባታቸው የማይመረትና በሽታው እንስሳቱን እየገደለ ያለ መሆኑ፣
- ኢንስቲትዩቱ በ2009 ዓ.ም የበግና ዳልጋ ከብት ኅሮረሳ፣ የፎዉል ኮለራ፤ የዶሮ Mycoplasma Gallisepticum፤ የከብቶች ጉርብርብ በሽታ እና Epizootic Lympangitis ለማሻሻል ጥናት ለማከናወን ታቅዶ ያልተከናወኑ መሆኑ፣
- የአባ ሠንጋና ኅሮርሳ ክትባቶችን ለግመል ስታንዳርዳይዝ ለማድረግ የበሽታ አምጭ ተህዋስያን የመለየትና ማደራጀት ሥራ ለማከናወን ታቀዶ የተጀመረ ቢሆንም ያልተጠናቀቀ መሆኑን፣

በኦዲቱ ወቅት በኢንስቲትዩቱ ከተከለሱት ማስረጃዎችና የመስክ ለባለሙያዎች ለቀረበላቸው መጠይቅ ከሰጡት መልስ ለመረዳት ተችሏል፡፡

63. ስለሁኔታው የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራአስኪያጅ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ በሽታው በቂ መረጃ የሌላቸውና የመቆጣጠሪያው ዘዴውም በክትባት ብቻ ሊሆን እንደሚችልና በሽታው በሃገሪቱ ውስጥ መኖሩን፣ ምን ዓይነት ህዋስ /strain/ እንዳለው የተመረጠው የመቆጣጠሪያ ስልት ምን እንደሆነ በሚመለከታቸው አካል ያልተረጋገጠ መሆኑን፣ ሌሎች የምርምር ሥራዎች በአንድ ጊዜ የማይጠናቀቁ በመሆናቸው በሂደት ላይ ያለ መሆኑን እና የአባ ሠንጋና ጎሮርሳ ክትባቶችን ለግመል ስታንደርዳይዝ የማድረጉ ሥራ የቅንጅትና የትኩረት ማነስ በመሆኑ በቅርቡ ሥራው የሚጠናቀቅ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

64. በየጊዜው የሚከሰቱትን የእንስሳት በሽታ ፍንዳታዎች ላይ ጥናትና ምርምር በማድረግ በክትባቱ አፋጣኝ ምላሽ ካልተሰጠ በእንስሳት ሀብት ላይ ጉዳት በማድረስ የህብረተሰቡ ኢኮኖሚ እንዲናጋ ከማድረጉም ሌላ የእንስሳት ሀብቱ ለግብርናው ኢኮኖሚ የበኩሉን ሚና እንዳይጫወት ያደርጋል፡፡

### የሚመረቱት ክትባቶች የሃገሪቱን ፍላጎት አሟልቶ ወደ ውጭ መላካቸውን በተመለከተ፡-

65. በኢንስቲትዩቱ የሚመረቱ የክትባት ምርቶች በቅድሚያ የሃገሪቱን ፍላጎት ሳያሟሉ ወደ ውጭ አገር መላክ የለባቸውም፡፡

66. ይሁን እንጂ የእብድ ውሻ (Rabesi)፤ አፍታ (FMD)፣ የፍየሎች ሳንባ (CCPP) መከላከያ የክትባት ምርቶችና የሳላይን ዉሃ የአገር ውስጥ ፍላጎት ሳይሟላ ወደ ውጭ ሀገር የሚላኩ መሆኑን በኢንስቲትዩቱ ከተከለሱት መረጃዎችና በኦሮሚያ፣ በአማራ፣ በደቡብ ብ/ብ/ሕ እና በአፋር ክልሎች በናሙና ተወስዶ በመስክ ለባለሙያ መጠይቅ በማቅረብ ከተሰጡት ምላሾች ለመረዳት ተችሏል፡፡

67. ጉዳዩ የሚመለከታቸው የክትባት ማምረቻና ሥርጭት የሥራ ክፍል ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ከሀገር ውጭ ያሉት የኢንስቲትዩቱ ደንበኞች በርካታ መጠን ያላቸው ሌሎች ክትባቶችን በሚገዙበት ወቅት የተጠቀሱትን ክትባቶች እንደተጨማሪ ስለሚጠይቁን ደንበኛ ለመያዝና ምርቱን ለማስተዋወቅ ለአንድ ጊዜ ብቻ በጥቂት ዶዝ ሽያጭ የተከናወነ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራአስኪያጅ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ የተጠቀሱት ክትባቶች የውጭ ሀገር ፍላጎት በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ በሀገሪቱ ውስጥ ያለውን ፍላጎት በድሎ ወደ ውጭ የተላከበት ሁኔታ የሌለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

68. የኢንስቲትዩቱ ኃላፊዎች ለአንድ ጊዜ ብቻ በጥቂት ዶዝ ሽያጭ እንደተከናወነ እና በሀገሪቱ ውስጥ ያለውን ፍላጎት በድሎ ወደ ውጭ የተላከበት ሁኔታ እንደሌለ የገለጹ ቢሆንም ከላይ የተጠቀሱት ክትባቶች በ2008 እቅድ ሣያቅዱ የአፍታ በዶዝ 25000 በብር 321341 እና በ2009 የአፍታ በዶዝ 27000 በብር 378270.90፣ የእብድ ውሻ መከላከያ ክትባት በዶዝ 10000 በብር 156508 በሁለቱ በጀት ዓመት ወደ ውጪ የተላኩ መሆኑን ከተከለሱ ማስረጃዎች የተረዳን በመሆኑ እንዲሁም በሀገር ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ የሚፈለጉ እና እጥረትም የታየባቸው በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

69. ኢንስቲትዩቱ የተቋቋመበት ዋና ዓላማ የእንስሳት ክትባትን በማምረት የሀገሪቱን እንስሳት ከበሽታ በመጠበቅ የእንስሳት ሀብቱ ለአገሪቱ ኢኮኖሚ የበኩሉን ሚና እንዲጫወት ማድረግን ተሳቢ አድርጎ የተቋቋመ የልማት ድርጅት በመሆኑ የሀገሪቱን ፍላጎት ሳይሟላ ወደ ውጭ የሚላክ ከሆነ የአገሪቱን እንስሳት ጤናማ ለማድረግ የሚደረገው ጥረት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ይፈጥራል፡፡

**የተለያዩ ኬሚካሎችና ክትባቶች አያያዝ፣ አጠቃቀም እና አወጋገድ መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፡-**

70. ኢንስቲትዩቱ የሚጠቀምባቸውን የተለያዩ ኬሚካሎች አያያዝ፣ አጠቃቀምና የተበላሹና ጊዜ ያለፈባቸዉ የክትባት ምርቶችን ጨምሮ የሚወገድበት የንብረት አያያዝና የአወጋገድ መመሪያ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት አዘጋጅቶ በማጸደቅ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

71. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት

- ኢንስቲትዩቱ ጥቅም ላይ ያልዋሉና ጊዜ ያለፈባቸው የክትባት ምርቶች አያያዝ፣ አጠቃቀምና የአወጋገድ መመሪያ ያላዘጋጀ መሆኑ፣
- በየወረዳው ጥቅም ላይ ያልዋሉና ጊዜ ያለፈባቸዉ የክትባት ምርቶች ሳይወገዱ ለዓመታት የተጠራቀሙ መሆኑ፣
- አንዳንድ ወረዳዎች ደግሞ ክትባትን የንብረት አወጋገድ መመሪያን ተጠቅመው እንደማንኛውም አካባቢ የማይጎዳ ንብረት በመቁጠር የሚያስወግዱመሆኑ፣
- በኢንስቲትዩቱ ክትባት ማምረቻ ክፍል ውስጥ ካልሽም ክሎራይድ እና የተለያዩ ባይሎጅካሎች ከ15 ዓመት በላይ የተቀመጡ መሆኑ፣
- በኢንስቲትዩቱ የተበላሹ ኬሚካሎች ማጠራቀሚያ መጋዘን/ስቶር ውስጥ ለብዙ ዓመታት ቤቱ አብሮ እስኪዝግ ደረስ የተቀመጡ ኬሚካሎች ያሉ መሆኑን፣

በኢንስቲትዩቱ ከተከለሱት ሰነዶችና በመስክ በተደረገው ምልከታ ለማወቅ ተችሏል፡፡

72. ስለሁኔታው የሚመለከታቸው የየወረዳው የሥራ ባለሙያዎች ተጠይቀው ክትባቶቹን ያመረተው ኢንስቲትዩቱ ክትባቶቹ እንዴት እንደሚወገዱ የሚያስረዳ መመሪያ ወይም መግለጫ አዘጋጅቶ አብሮ ከክትባቶቹ ጋር ባለመላኩ ለማስወገድ መቸገራቸውን በቀረበላቸው ቃለመጠይቅ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

73. ስለጉዳዩ የኢኒስቲትዩቱ የሥራ ክፍል ኃላፊዎች ተጠይቀው፡-

- በኢንስቲትዩቱ የሚመረቱ የክትባት ምርቶችን ለማስወገድ ኢንስቲትዩቱ የራሱ የሆነ የአሠራር ማንዋል (SOP) ያለው በመሆኑ ከውጭ ሀገርም ሆነ ከአገር ውስጥ ሰብስበው ያመጡትን የሚያስወግድ ቢሆንም ክትባት በተሠራጨበት አካባቢ ሁሉ ባለሙያዎች በራሳቸው እንዲያስወግዱ አንስቲትዩቱ መመሪያ አለመስተላለፉ እንደ ክፍተት መውሰድ የሚቻል መሆኑን፣
- ኬሚካልን በተመለከተ በሀገሪቱ ውስጥ የኬሚካል አወጋገድ መመሪያ ባለመኖሩ የተፈጠረ ክፍተት መሆኑንና በአሁኑ ወቅት ከአካባቢ አየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር ጋር ለማስወገድ እየተሠራ መሆኑን
- ክትባቶቹን ለማስወገድ ችግር ያለባቸው ወረዳዎች ክትባት ለመውሰድ ሲመጡ የተጠቀሙበትን የመያዣ ብልቃጦች (Vialies) እንዲመልሱ እየተነገራቸው መሆኑን

በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በቀርቦላቸው መጠይቅ በሰጡት ምላሽ ላይ የገለፁ ቢሆንም በመስክ ላይ ተበላሽቶ ስለተከማቸ ክትባት ምንም ዓይነት ምላሽ አልሰጡም፡፡

74. በኢንስቲትዩቱ የተመረቱት ክትባቶችም ሆነ ከሌላ ሀገር ለክትባት ማምረቻ የሚጠቀሙበት ኬሚካል መመሪያ ተዘጋጅቶለት በመመሪያው መሠረት የማይወገድ ከሆነ አካባቢውን በመመረዝ በሰውና በእንስሳት ጤንነት ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡

**ክትባቶች ሲመረቱም ሆነ ከተመረቱ በኃላ የምርት ብክለትና ብክነት ሣይኖር ጥራታቸውን ጠብቀው ለተጠቃሚ መድረሳቸውን በተመለከተ፡-**

75. ክትባቶች ሲመረቱም ሆነ ከተመረቱ በኋላ የምርት ብክለትና ብክነት እንዳይኖር ኢንስቲትዩቱ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመነጋገር ምርቱ

ከሚፈልገው የኤሌክትሪክ ኃይል ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የኤሌክትሪክ ጉልበት እንዲዘጋጅ ሊያርግ ይገባል፡፡

76. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በኢንስቲትዩቱ ከተከለሱት ማስረጃዎችና በመስክ ለባለሙያዎች ለቀረበላቸው መጠይቅ ከሰጡት መልስ ለመረዳት እንደተቻለው፡-

- ከ2007-2009 ዓ.ም ብቻ ኢንስቲትዩቱ በብክለት/ብክነት ምክንያት 55,547,099 ዶዝ ክትባት በብር 16,969,597 ያጣ መሆኑ፤
- በኤሌትሪክ ኃይል እጥረት/መቆራረጥ/ ምክንያት የማምረቻ መሣሪያዎቹ ለብልሽት የሚደረጉ መሆኑ፣
- በየወረዳዎች በመብራት መቆራረጥ ምክንያት ክትባቶች ለብልሽት የሚደረጉ መሆኑ፣
- በመብራት መቆራረጥና እጥረት የተነሳ ከ2007 እስከ 2009 በጀት ዓመት ለጄኔሬታር ነዳጅ ግዥ ብር፡ 3,003,878.67 /ሶስት ሚሊዮን ሶስት ሺ ስምንት መቶ ሰባ ስምንት ብር/ ያወጣ መሆኑ፤ ታውቋል፡፡

77. ስለሁኔታው የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ በመብራት መቆራረጥ ምክንያት በምርት ሂደት ላይ የክትባት ብክለት በመከሰቱ የተፈጠረ በመሆኑ የመብራት ችግር እስከልተፈታ ድረስ ብክለትን መቅረፍ አስቸጋሪ መሆኑን አስረድቷል፡፡

78. የኢንስቲትዩቱ ኃላፊዎች ስለ ኤሌትሪክ መቆራረጥ ችግር እንጂ የኤሌትሪክ ኃይል እጥረት/ማነስን በተመለከተ መልስ አልሰጡም፡፡ የገጠማቸውን የኃይል ማነስ በተመለከተም ችግሩ እንዲፈታላቸው የሚመለከተውን መስሪያ ቤት ሆነ ተጠሪ ለሆኑበት ሚኒስቴር መ/ቤት ያሳወቁበትን ወይም የጻፉትን ደብዳቤና የደረጉትን ክትትል የሚያሳዩ ማስረጃዎች ያልቀረቡ በመሆኑ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል አስቸጋሪ ነው፡፡

79. ኢንስቲትዩቱ ለክትባት ምርት አስፋላጊ የሆነውን የመብረት መጠን ከልተመቻቸ በየዓመቱ በሚሊዮን ዶዝና ብር የሚቆጠር የክትባት ብክለትና ብክነት ከመከሰቱም በላይ ለጄኔሬተር ነዳጅ ግዥ በየዓመቱ ብዙ ሚልዮን ብር እንደሚወጣ እንዲሁም ውድ የሆኑ የማምረቻ መሣሪያ ብልሽት በመከሰት ከፍተኛ ወጭ እንዲወጣ በማደርግ በኢንስቲትዩቱ ትርፋማና ውጤታማነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡

ንብረቶች ሲበላሹ ቶሎ ተጥግነዉ ወደ ሥራ የሚገቡ መሆኑን በተመለከተ፡-

80. የክትባት ምርት ማምረቻ መሣሪያዎች ሲበላሹ ቶሎ ተጥግነዉ ወደ ስራ የሚገቡበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

81. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በኢንስቲትዩቱ በተለያዩ የክትባት ማምረቻ ክፍሎች 2 ላሚናር ፍሎዉ(Laminar Flow)፣ አንድ እንኩቤተር( inoculators፣ አንድ ድራይ ኦቫይን (Dryovine)፣ አንድ ፍሎሬሰንት ማይክሮስኮፕ(Filoracent Microscop)፣ አንድ የዶሮ ክትባት ማምረቻ (Egg inoculators & Harvestor) ከቫክ ናዳል ድርጅት በእርዳታ የተገኘ እና ሌሎችም ንብረቶች ከ6 ወር እስከ 3 ዓመት ሳይጠገኑ የተቀመጡ መኖራቸውን በየማምረቻ ክፍሎች በተደረገው ምልከታ ለማወቅ ተችሏል፡፡

82. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የክትባት ማምረቻና ሥርጭት የሥራ ክፍል ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ የተጠቀሱት ንብረቶች ተበላሽተው ጥገና ሊደረግላቸው ያልቻለበት ምክንያት የመለዋወጫ አካላቸው ባለመገኘቱ እና አንዳንዶቹ ደግሞ ከኢንስቲትዩቱ የጥገና ባለሙያ አቅም በላይ በመሆናቸው ለብዙ ጊዜያት ሳይጠገኑ የቆዩ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

83. ስለሁኔታው የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራአስኪያጅ ተጠይቀው

- ሁለት ለሚናር ፍሎ upon delivery መስታወታቸው በመሰበሩ እስኪተካ እየተጠበቀ መሆኑን፣
- ኢንኩቤተርና ድራይ ኦቨን የላብራቶሪ ማስፋፉያ እስኪጠናቀቅ የተቀመጡ መሆናቸውን እና
- የዶሮ ክትባት ማምረቻ (Egg inoculators & Harvestor) ከቫክ ናዳል ድርጅት በእርዳታ የተገኘውን ለመጠቀም ቴክኖሎጂው አዲስ በመሆኑ ፈጥኖ መጠቀም ፍራቻ በመኖሩ እንደሆነና በአሁኑ ወቅት ግን የቫሊዴሽን ሥራ በመሥራት ወደ ሥራ ሊገቡ እንደሆነ

በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ላይ አስረድተዋል፡፡

84. እንስቲትዩቱ የማምረቻ መሣሪያዎች ስበላሹ ቶሎ ተጠግነው ወደ ሥራ የማይገቡ ከሆነ የማምረቻ መሣሪያዎች ካለው በየጊዜ የዋጋ ጭማሪ የተነሳ በቀላሉ ለመተካት ሰለማይቻል በኢንስቲትዩቱ ትርፋማነት አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡

## የአካባቢና የባለሙያ ደህንነት የሚጠብቅ የአሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፡-

85. በኢንስቲትዩቱ የአካባቢና የባለሙያ ደህንነት የሚጠብቅ የአሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

86. ይሁን ኢንጂ በሚድያ ዝግጅት ላብራቶሪ ክፍል፡-

- ክፍሉ ጠባብና ሙቀት ያለው ሲሆን ለሠራተኞች የሙቀት መጠን ማስተካከያ (ኤሲ) ወይም ቬንትለተር የሌለው መሆኑ፣
- ከሚካል ሁድ የሚባል ለኬሚካል ንክኪ መከላከያ ለሠራተኞች ጤንነትና ደህንነት አስፈላጊ ሲሆን ያልተሟላ መሆኑ፣
- በየክትባት ማምረቻ ክፍሎች ለክትባት ብክለት መከላከያ ለጤና ጠንቅ የሆኑትን ጨረር የሚጠቀሙ ሲሆን የጨረር መጠን በሰው ጤና ላይ ጉዳት የማያደርስ መሆኑን በሚመለከታቸው አካል እንዲረጋገጥ ያላደረጉ መሆኑና በትክክለኛው መንገድ ለመከላከል አስቸጋሪ መሆኑ፣
- ኢንስቲትዩቱ በ2009 ዓ.ም በሙያ ደህንነትና ጤንነት፣ በስራ ቦታና አካባቢ አያያዝ ላይ የልምድ ልውውጥ ለማደረግ ያቀደ ቢሆንም ያልተከናወነ መሆኑን፣

በኢንስቲትዩቱ ከተከለሱት ማስረጃዎችና በየማምረቻ ክፍሎቹ በተደረገው ምልከታ ለመረዳት ተችሏል፡፡



በክፍሉ የክትባት መያዣ ዕቃ ስትራላይዝ የሚደረግበት በመሆኑ ከፍተኛ ሙቀት ያለው ከመሆኑም በተጨማሪ የክፍል ጥበት በመኖሩ ዕቃው ከቦታቦታ እየተገፋ ሥራ የሚያከናውኑ መሆኑን የሚያሣይ

87. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የክትባት ማምረቻና ሥርጭት የሥራ ክፍል ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ አሁን እየተጠቀሙበት ያለው ፎርማሊንና ጨረር መጠን በሰው ጤና ላይ ጉዳት የሚያደርስ አለመሆኑንና በክትባት አመራረት ሂደት

የተጠቀሱት ኬሚካሎችና ጨረር ማስወገድ የማይቻል ባለመሆኑ አጠቃቀሙን ሠራተኛው ሥራ ከመጀመሩ በፊት አብርቶ ጨረር አጥፍቶ ስለሚጠቀሙ በሰው ላይ ያደረሰው ችግር እስከ አሁን የሌለ መሆኑ፤ ነገር ግን ይህን የሚተካ ሌላ አማራጭ ለመጠቀም በዓለም ላይ የተጠናና የተወሰደ ተሞክሮ የሌለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

88. ስለሁኔታው የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ በሚዲያ ዝግጅት ክፍል ያለው ላብራቶሪ ለAC መግጠሚያ አመች ባለመሆኑ እንደሆነ፣ ከሚካል ሁድ ያስፈልጋል ለተባሉት ክፍሎች 2 ተገዝቶ የቀረበላቸው መሆኑን፣ የሥራው ፀባይ ባይሆንም ለክፍሉ ሠራተኞች ወተት በነፃ እንዲያገኙ እየተደረገ መሆኑን እና በሙያ ደህንነትና ጤንነት፣ በስራ ቦታና አካባቢ አያያዝ ላይ የልምድ ልውውጥ ለማደረግ ባለሙያው የካይዘን አፊሰር በመሆኑ ካይዘንን ለማስተግበር የሥራ መደራረብ በመኖሩ ዕቅዱን ማከናወን ያልተቻለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

89. የኢንስቲትዩቱ ኃላፊዎች አሁን እየተጠቀሙበት ያለው ፎርማሊንና ጨረር መጠን በሰው ጤና ላይ ጉዳት የማያደርስ አለመሆኑን ከሚመለከተው መስሪያ ቤት ጉዳት የማያደርስ ስለመሆኑ የተረጋገጠበት ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል አስቸጋሪ ነው፡፡

90. በክትባት ማምረት ሂደት በአካባቢና በሰው ጤና ለይ ተፅዕኖ የሚያሳደሩ ጨረርና ፎርማሊን በሌላ አማራጭ ከልተተካ በአሁኑ ወቅት እየተስፋፋ ባለው የካንሰር በሽታ ሊያጋልት ይችላል፡፡

### የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ክፍተትን በመለየት ለባለሙያዎች ስለጠና መሰጠቱን በተመለከተ፡-

91. ኢንስትቲዩቱ የአመራረት እና የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ክፍተትን በመለየት ለባለሙያዎች ስልጠና የሚሰጥበትን ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

92. ኢንስቲትዩቱ ለሰራተኞች የትምህርት እድል እንዲያገኙና እራሳቸውን እንዲያበቁ የሚያደርግ ቢሆንም ሥራን መሠረት ያደረገ ክፍተት በመለየት የአጫጭር ጊዜ ስልጠና እንዲያገኙ ያልተደረገ መሆኑን የኢንስቲትዩቱ ባለሙያዎች ከሰጡት አስተያየት ለመረዳት ተችሏል፡፡

93. ጉዳዩ የሚመለከታቸው የክትባት ጥራት ማረጋገጫ አገልግሎት የሥራ ክፍል ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ሥራን መሠረት ያደረገ አጫጭር ሥልጠናዎች ተከታታይነት ባለው መልኩ ለባለሙያው ለባለ ድርሻ አካላት ቢሠጥ የተሸለ መሆኑን አስረዷቷል፡፡

94. ስለሁኔታው የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራአስኪያጅ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ተቋሙ በዓመት አራት የምርት ሠራተኞችን እያስተማረ ከዲፕሎማ እስከ ማስተርስና ፒኤች ዲ ያደረሰ መሆኑን የገለፁ ቢሆንም ሥራን መሠረት ያደረገ አጫጭር ሥልጠናዎችን በተመለከተ ምንም ምሽ አልሰጡም፡፡

95. ኢንስቲትዩቱ ለምርት ሠራተኞች ሥራን መሠረተት ያደረግ አጫጭር ስልጠናዎች ካልሰጠ ከቀን ወደ ቀን የሚሻሻለውን የተክኖሎጂ አጠቃቀም ላይ ውስንነት ሊያጋጥም ይችላል፡፡

## ክፍል ሶስት

## የመደምደሚያ ሃሳቦች

96. የእንስሳት ክትባትና ሪኤጀንቶችን ማምረት፣ መድኃኒቶችን ማቀነባበር እና አያያዝ ሥርዓት አፈፃፀም ውጤታማ በሆነ መልኩ መከናወኑን እና የታሰበውን ዓላማ ማሳካት የተቻለ መሆኑን በተመለከተ የሚከተሉት የአሠራር ግድፈቶች እና ክፍተቶች መኖሩን የሚከተሉት መደምደሚያ ሃሳቦች ላይ ተደርሷል፡-

- የክትባት ማምረቻ ክፍሎቹ የመልካም አመራረት ዘዴን ((Good Manufacturing Practices) ስለሌለው የክትባት ምርቱን የመልካም አመራረት ዘዴን ሰርተፊኬት ለሚጠይቁ አገሮች ተወዳድሮ ለመሸጥ የማያስችል መሆኑ፣
- ኢኒስቲትዩቱ የአገሪቱንና የውጭ አገር ፍላጎት ጋር የተመጣጠነ የክትባት ምርት ማቅረብ ያልቻለ መሆኑ፣
- ኢኒስቲትዩቱ የክትባት ማሰራጫ ጣቢያዎች ያላቋቋመ መሆኑ፣
- ከ2002 ዓ.ም ጀመሮ ግንባታቸው የተጀመሩ ቀዝቃዛ መጋዘኖችን /Cold Room/ ሥራ ያልተጠናቀቁ መሆኑ፣
- የተጀመሩት 13 ቀዝቃዛ መጋዘኖች በባለቤትነት የሚከታተላቸው አካል ባለመኖሩ ሣር እየበቀለበት፣ ፀሀይ፣ ዝናብና ንፋስ እየተፈራረቀባቸው በመፈራረስ ለአደጋ የተጋለጡ መሆኑ፣
- ቅድሚያ ክፍያ 30% ተፈፀሞ ግንባታቸው ያልተጀመሩ ሦስት ቀዝቃዛ መጋዘኖች መኖራቸው፣
- ቀዝቃዛ መጋዘኖች ከተጀመሩባቸው አካባቢዎች ውስጥ የቦታ ምርጫ የተጠቃሚዎችን ፈላጎት ያላገነዘቡ መኖራቸው፣
- ኢንስቲትዩቱ የቀዝቃዛ መጋዘኖቹ ግንባታ መቋረጡንና ለታለመለት ዓላማ አለመዋሉን ለሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ያላሳወቀ መሆኑ፣
- ለ16 ቀዝቃዛ መጋዘኖች ግንባታ ብር 11,417,315.80 እና ለዘጠኝ መጋዘኖች ኤሌክትሪክ ቆጣሪ ማስገቢያ ብር 671,884 በድምሩ ብር 12,089,199.80 ክፍያ ተፈፀሞ ለታለመለት ዓላማ ያልዋለ መሆኑ፣
- በኦሮሚያ ክልል ነገሌ ቦረና ጎጂ ዞን ይገነባል ተብሎ የተሰበው ቀዝቃዛ መጋዘን ምንም ዓይነት የተጀመረ ግንባታ ሣይኖር ለኤሌክትሪክ ቆጣሪ ማስገቢ/ማስገጠሚያ/ተብሎ ብር 98718 ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ፣

- ኢንስትቲዩቱ የደንበኞች ፍላጎት ያገናዘበ የአፍታ(FMD)፣ የፍየሎች ሳንባ (CCPP) የእብድ ውሻ፣ የግመል መከላከያ ክትባቶች እና የሳላይን ዉሃ በሚፈልጉት መጠንና ጊዜ አምርቶ የማይቀርብ መሆኑ፣
- የአፍታ(FMD) እና የእብድ ውሻ መከላከያ በሽታዎች ክትባቶች በአገሪቱ ውስጥ ከፍተኛ እጥረት እየለ ወደ ውጭ አገር የሚላኩ መሆኑ፣
- ኢንስትቲዩቱ የሚያቀርበው የአባጎረባ (Black leg)፣ አባሰንጋ (Anthrax) እና የጎሮርሳ (Bovine Pasteuellosis) የክትባት ምርቶች በህብረተሰቡ ፍላጎት መሠረት የመያዣ መጠን/ ዶዝ ከፋፍሎ የማይቀርብ መሆኑ፣
- ለክትባት ማምረቻ አገልግሎት የሚውሉ መሣሪያዎችና ግብዓቶች በወቅቱ የማይቀርቡ እና ከስፔስፊኬሽና ግዥ ማዘዣ ጋር ተገናዝቦ ገቢ የማይደረጉ መሆኑ፣
- በኢንስቲትዩቱ ለክትባት ማምረቻ ከውጭ አገር የሚቀርቡት ግብዓቶች ጥራት የሚረጋገጥበት ዘዴ የሌለ መሆኑ፣
- ኢንስትቲዩቱ የተለያየ የእንስሳት መድኃኒቶችን አቀነባብሮ ለተጠቃሚዎች ያላቀረበ መሆኑ፣
- ኢንስቲትዩቱ እያመረተ ለእንስሳት በሽታ መከላከያ የሚቀርባቸው ክትባቶች በተለያየ ምክንያት በሽታውን እያባሰባቸው ብሎም እየገደላቸው መሆኑ፣
- ኢንስቲትዩቱ በክትባት አያያዝና አጠቃቀም ዙሪያ ከሚመለከታቸው አካለት ጋር በቅንጅት በመሆን ለተጠቃሚው ተደራሽ በሆነ መልኩና ቋንቋዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ያልሰጠ መሆኑ፡-
- ስለክትባት ግንዛቤ የሚፈጥሩ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት በሬድዩ በተለያየ ቋንቋ የማስተዋወቅ ሥራ ያልተከናወነ መሆኑ፣
- በኢንስቲትዩቱ በጥናት የተደገፉ በአገር ውስጥ ለሚከሰቱ የእንስሳት በሽታች አዳዲስ ክትባቶችን የማውጣትና ነባር ክትባቶችን የማሻሻል ሂደት አዝጋሚ መሆኑ፣
- ኢንስቲትዩቱ ጥቅም ላይ ያልዋሉና ጊዜ ያለፈባቸው የክትባት ምርቶች አያያዝ፣ አጠቃቀምና የአወጋገድ መመሪያ አዘጋጅቶ ለተጠቃሚው ያላስተላለፈ መሆኑ፣
- ክትባቶች ሲመረቱም ሆነ ከተመረቱ በኃላ በብክለት/ብክነት ምክንያት ከ2007-2009 በጀት ዓመት 55,547,099 ዶዝ ክትባት በብር 16,969,597 ያጣ መሆኑ፤

- በመብራት መቆራረጥና እጥረት የተነሳ ከ2007 እስከ 2009 በጀት ዓመት ለጄኔሬታር ነዳጅ ግዥ ብር፡ 3,003,878.67 /ሶስት ሚሊዮን ሶስት ሺ ስምንት መቶ ሰባ ስምንት ብር/ ያወጣ መሆኑ፣
- በኢንስቲትዩቱ በተለያዩ የክትባት ማምረቻ ክፍሎች ተበላሽቶ ከ6 ወር እስከ 3 ዓመት ሳይጠገኑ የተቀመጡ የማምረቻ መሣሪያ መኖራቸው፣
- በኢንስቲትዩቱ ለክትባት ብክለት መከላከያ የሚጠቀሙት ጨረር መጠን ምን ያህል እንደሆነ በሚመለከተው አካል አለመረጋገጡና ሠራተኞቹን ለአደጋ የሚያጋልጥ መሆኑ፣
- ኢንስቲትዩቱ ለሰራተኞች ሥራን መሠረት ያደረገ ክፍተት በመለየት የአጫጭር ጊዜ ስልጠና እንዲያገኙ ያለደረገ መሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡

97. ስለሆነም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶች እና ችግሮችን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል ይረዳሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

## ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሃሳቦች

98. የእንስሳት ክትባትን ለማምረት፣ የተለያየ የእንስሳት መድኃኒቶችን ለማቀነባበር እና አያያዝ ሥርዓት ተከትለው እንዲተገበሩ ያስችላሉ ተብለው የታመነባቸው የማሻሻያ ሃሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ኢንስቲትዩቱ ለአገሪቱ ብቸኛ የክትባት አምራች ተቋም በመሆኑ የክትባት ማምረቻ ክፍሎች በመልካም አመራረት ዘዴን (GMP) በማደራጀት፣ እና በምርት ሂደትና ከተመረተ በኃላ የሚከሰቱ ብክለትና ብክነትን በመቀነስ የሃገሪቱን ፍላጎት ከማሟሟላት አልፎ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ሆኖ ወደ ውጭ ሀገር የሚላከውን የክትባት መጠን በማስፋት ለሃገሪቱ ተጨማሪ የውጭ ምንዛሬ ለማስገኘት የበኩሉን አስተዋጽኦ ሊያደረግ ይገባል፡፡
- ኢንስቲትዩቱ አማካይ በሆኑ የአገሪቱ አካባቢዎች የራሱ የሆነ የክትባት ማሰራጫ ጣቢያዎችን በማዘጋጀት የሚያመርታቸው ክትባቶች ለተጠቃሚው ሕብረተሰብ በቀላሉ የሚደርስበትን ሁኔታ ሊያመቻችና በማጓጓዝ የሚከሰተውን ብክነት ሊቀነስ ይገባል፡፡
- ከሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል አስፈጻሚ አካላት ጋር በመሆን ቀደም ሲል ብሔራዊ የአደጋ ሥጋት ዝግጁነትና ሥራ አመራር ኮሚሽን የተባለው በግብርና ሚኒስቴር ሥር በነበረበት ወቅት በተመረጡ የአገሪቱ አካባቢዎች ቀዝቃዛ መጋዘኖች /Cold Room/ አስገንብቶ ለተጠቃሚዎች ለማስተላላፍ ተብለው የተጀመሩትና ቅድሚያ ክፍያ የተከፈለባቸው 13 ቀዝቃዛ መጋዘኖች ግንባታቸው ተጀምሮ በአሁኑ ወቅት እየፈራረሰ ያሉ ያለና የሶስት ቀዝቃዛ መጋዝን ግንባታቸው ያልተጀመረውን እንዲጀመሩና ተጠናቀው ወደ ሥራ የሚገቡበትን ሁኔታ በማመቻቸት ወደ ሥራ እንዲገቡ በማድረግ ለታለመላቸውት ዓለማ እንዲውሉ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ይህንንም በማድረግ ኢንስቲትዩቱ እያመረተ ለእንስሳት በሽታ መከላከያነት የሚቀርባቸው የክትባት ምርቶች በተለያየ አካባቢ ከማጓጓዝ፣ በአከመቻቸትና አጠቃቀም ጉድለት ምክንያት በእንስሳት ላይ ጉዳት እያደረሰ በህብረተሰቡ ዘንድ ቅሬታ የፈጠሩበትን ምክንያት በጥናትና ምርምር በመፈተሽ የህብረተሰቡ ችግር ሊፈታ ይገባል፡፡

- ኢንስትቲዩቱ በአገሪቱ ወስጥ ያሉትን የእንስሳት በሽታ በጥናት በመለየት የደንበኞች ፍላጎት ያገናዘበ የመከላከያ ክትባት ምርት በዓይነት፣ በመጠን፣ በጊዜ እና በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ የበሽታ ስርጭት እንዲቀንስ በማድረግ የእንስሳት ሀብቱ ለአገሪቱ የግብርና ኢኮኖሚ የበኩሉን አስታወፅኦ እንዲያበረክት ሊያደርግ ይገባል፡፡ እንዲሁም የእብድ ውሻ በሽታ ከሰው ጤና አንፃር፣ የአፍታ እና የአባጎረባ (Black Leg) ክትባቶች ዋጋቸው የህብረተሰቡን አቅም ያገናዘበ እንዲሆን ለማድረግ ለእንስሳትና አሳ ሀብት ሚኒስቴር አማራጭ መፍትሔዎችና አጥንቶ ሊያቀርብ ይገባል፡፡
- ኢንስቲትዩቱ ለክትባት ማምረቻ አገልግሎት የሚውሉ መሣሪያዎችንና ግብዓቶችን ጥራታቸው የሚረጋገጥበት ሥረዓት በመዘርጋት ሙያን የሚጠይቁ የግዥ መጠየቂያዎች በባለሙያ እንዲያዘጋጅና ገቢ ሲደረግም ከማዘዣ ጋር እየተመሳከረ እንዲገባ በማድረግ በአቅርቦት ላይ የሚከሰቱ የሀብት ብክነቶች እንዳይኖር የተጠናከረ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡
- በኢንስቲትዩቱ በሪኤጀንቶችና ንብረት ማከማቻ መጋዘን ውስጥ በ18/11/05 ዓ.ም 70.5 ኩንታል 7938 USD ተገዝቶ ገቢ የተደረገው ALUMINIUM HYDROXID GEL የሚባል ኬሚካል እስከ አሁን አንድ ኩንታል ብቻ አገልግሎት ላይ የዋለ በመሆኑና በአሁኑ ወቅት 69.5 ኩንታል በመጋዘን ውስጥ ሆኖ የመጠቀሚያ ጊዜዉ በታህሳስ 2011 የሚያበቃ በመሆኑ አፋጣኝ እርምጃ በመውሰድ የመጠቀሚያው ጊዜ ሳያልፍ አገልግሎት ላይ የሚውልበት ምቹ ሁኔታ ሊፈጥር የገባል፡፡
- ኢንስትቲዩቱ የተለያየ የእንስሳት መድኃኒቶችን ለማቀነባበር የጀመረውን የህንፃ ግንባታ በፍጥነት እንዲጠናቀቅ በማድረግ አገሪቱ ለእንስሳት መድኃኒት ግዥ የሚታወጣውን የውጭ ምንዛሪ እንዲቀነስ፣ በአገራችን ውስጥ በእንስሳት እርባታ የሚተዳደሩ ተጠቃሚው አርሶ አደር፣ አርብቶ አደር እና ከፊል አርብቶ አደር ጥራቱን የጠበቀ የእንስሳት መድኃኒት በዓይነት፣ በመጠን እና በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኙ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኢንስቲትዩቱ በክትባት አያያዝና አጠቃቀም ዙሪያ ከሚመለከታቸው ባድርሻ አካለት ጋር በቅንጅት በመሆን በማድረግና ለተጠቃሚው የግንዛቤ ማስጨበጫ በመስጠት በተለያየ አካባቢዎች በአያያዝ ምክንያት ለብልሽት የሚደረጉ

የእንስሳት መከላከያ ክትባቶች እንዳይኖሩ በማድረግ ጥራተቸውን ጠብቀው ለእንስሳቱ እንዲሰጥ ሊያደርግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ኢንስቲትዩቱ ነባር ክትባቶች ስለመሻሻላቸውና አዳዲስ ክትባቶች ስለመፈጠራቸዉ በክልል፣ በዞንና ወረዳ ላይ ያሉት ባለሙያዎች የሚያሳውቅበት የአሠራር ሥረዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ኢንስቲትዩቱ ክትባትን በተመለከተ ከእንስሳት አርቢው የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር የልምድ ልውውጥና ውይይት የሚያደረግበትን እንዲሁም ክትባትን በተመለከተ ከህብረተሰቡ የሚነሱ ችግሮች የሚለይበትን መድረክ መደበኛ በሆነ መልኩ የሚዘጋጅበት የአሠራር ሥረዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ የእንስሳት በሽታን ቅድመ መከላከል ሥራ የሚያግዝ የአገሪቱ የእንስሳት ክትባት ፖሊሲ ወይንም ሥትራቴጂ እንዲዘጋጅ ከእንስሳትና አሳ ሀብት ሚኒስቴር ጋር በመሆን የራሱን ድርሻ ሊወጣ ይገባል፡፡


- ኢንስቲትዩቱ የክትባት አያያዝና አወጋገድ መመሪያ በማዘጋጀትና ለተጠቃሚው ደንበኞች በማሰራጨት በየክልሉ፣ በየዞንና ወረዳ ተበላሽቶ የተቀመጡ የክትባት ምርቶች እንዲወገዱ ሊያደርግና ወደፊትም ክትባቶቹ ሳይበላሹ ሥራ ላይ የሚውሉበትን መንገድ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር መፍትሔ ሊያስቀምጥ ይገባል፡፡
- ኢንስቲትዩቱ ስለክትባት ግንዛቤ የሚፈጥሩ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት በሬድዩ/ቴሌቪዥን ህብረተሰቡ ሊረዳው በሚችል እና ተደራሽ በሆነ መልኩ በተለያየ ቋንቋ በማስተዋወቅ ህብረተሰቡ ስለክትባቱ በቂ ግንዛቤ እንዲኖረው ምቹ ሁኔታ ሊፈጥር እና አሁን የጀመረውን አጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል፡፡
- በኢንስቲትዩቱ ከሚመረቱት የክትባት ምርቶች ውስጥ የፍያሎች ሣንባ (CCPP)፣ የአፍታ (FMD) እና የእብድ ውሻ (Rabies) በሽታ መከላከያ ክትባቶችና የሳላይን ውሃ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር ከፍተኛ ፍላጎት ያላቸው ሆኑ በበቂ ሁኔታ የማይመረቱ በመሆኑ ምርቱ የሚጨምርበትና የአገሪቱን ፍላጎት በማሸነፍ ከውጭ ምንዛሪ የሚያስገኙበት ምቹ ሁኔታ ሊፈጥር ይገባል፡፡
- ኢንስቲትዩቱ የሚያመርታቸው የክትባት ምርቶች በዋናነት በአገሪቱ ውስጥ የሚከሰቱ የእንስሳት በሽታ ለመከላከል አልፎም ከተቻለ ለማጥፋት ዓለማ ተይዞ በመንግስተ የተቋቋመ በመሆኑ የክትባት ምርቱ በአገሪቱ ውስጥ ያለውን

ፍላጎት ለማሟላት ቅድሚያ በመስጠት የህበረተሰቡን ፍላጎት ለማሟላት እና ወደ ውጭ ከሚለካው ቅድሚያ ሊሰጥ ይገባል፡፡

- በኢንስቲትዩቱ ክትባቶች ሲመረቱም ሆነ ከተመረቱ በኃላ በየዓመት በሚልዮን የሚቆጠሩ በዶዝና በብር የክትባት በብክለት/ብክነት በተለያየ ምክንያት የሚከሰት ከመሆኑም በላይ በመብራት መቆራረጥን ለማስወገድ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር አፋጣኝ መፍትሔ በመፈለግ ለመጠባበቂያ ጄኔሬተር የሚያወጣውን ወጪ የሚቀንስበትን ሁኔታ ሊያመቻች ይገባል፡፡
- ኢንስቲትዩቱ ለክትባት ማምረቻ የሚጠቀማቸው መሣሪያዎችን መደበኛ ጥገና የሚያገኙበት እንዲሁም ሲበላሹ በአፋጣኝ ተጠግነው አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ ማድረግ የሚያስችል አሠራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ለአገሪቱም ሆነ ለኢንስቲትዩቱ ትልቁ ሀብት የሰው ኃይል በመሆኑ በየማምረቻ ክፍሎቹ ለብክለት መከላከያ የሚጠቀሙት ጨረር መጠን ምን ያህል እንደሆነ ሥልጣን በተሰጠው አካል እንዲረጋገጥ በማድረግ ሠራተኞቹን ከአደጋ የሚከላከልበትን ሁኔታ ሊያመቻች ይገባል፡፤ በተጨማሪም በክትባት ማምረቻ ክፍሎች ውስጥ የሚከሰተውን ከፍተኛ ሙቀት በሠራተኞቹ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ስለሚያሳድር ይህን ለማስወገድ የሚያስችል አፋጣን የመፍትሔ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡
- የሚካናውናቸውን ሥራዎች ለማቀላጠፍ እንዲረዳው ኢንስቲትዩቱ በጥናት ላይ የተመረኮዘ እና ሥራን መሠረት ያደረገ የሠራተኞቹን ክፍተት በመለየት የአጫጭር ጊዜ ስልጠና ባለሙያዎች እንዲያገኙ በማድረግ የአመራረት ሂደቱ እንዲሻሻል ሊያደርግ ይገባል፡፡

በመጨረሻም የብሔራዊ የእንስሳት ጤና ጥበቃ ኢንስቲትዩት፣ የብሔራዊ የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን፣ በናሙና ተመርጠው የታዩ የክልሎች፣ የዞኖችና የወረዳዎች የእንስሳትና ሀብት የቢሮዎችና የጽ/ቤቶች የሥራ ኃላፊዎች እና ሰራተኞች በኦዲቱ ወቅት የተጠየቁትን መረጃዎች በወቅቱ በማቅረብና ለቀረቡ ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ በመስጠት ስለተደረገልን የሥራ ትብብር ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡

## አባሪ- 1 ፡የኢንስቲትዩቱ መዋቅራዊ አደረጃጀት መግለጫ፡-



## አባሪ 2፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria

| የኦዲት ጭብጥ | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት |
|---|---|
| ፩. የእንስሳት ክትባት፣ ባዮሎጂካሎችና ሪኤጀንቶችን በማምረት እና መድኃኒቶችን የማቀነባበርና ተደራሽ የማድረጉ ሥራ ውጤታማ ስለመሆኑ መገምገም፡ | 1. የክትባቶች አመራረት ቴክኖሎጂ ቀልጣፋ፤ ዉጤታማና የሃገሪቱን ፍላጎት አሟልቶ ወደ ዉጭ ሀገር በመላክ የዉጭ ምንዛሬ ለሃገሪቱ የሚያስገኝ ሊሆን ይገባል፡፡ |
| | 2. ኢንስቲትዩቱ ክትባቶችን ለተጠቃሚው ህብረተሰብ ለማዳረስ እንዲችል በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የሽያጭ ቢሮችንና የክትባት ማቆያ ማጋዘኖችን /Cold Room/ ከሚመለከተው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት አዘጋጅቶ አገልግሎት ላይ እንዲውል ሊያደረግ ይገባል፡፡ |
| | 3. ኢንስቲትዩቱ የደንበኞች ፍላጎት ያገናዘበ የክትባት ምርት በዓይነት፣ በመጠንና በጊዜ በማቅረብ የተጠቃሚዎችን ፍላጎት ሊያሟላ ይገባል፡፡ |
| | 4. ለክትባት ማምረቻ አገልግሎት የሚውሉ ግብዓቶች በሚፈለገው መጠን፣ ጥራትና ጊዜ የሚቀርብበት ቀልጣፋና ተጠያቂነት ያለው የአሠራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 5. ኢንስቲትዩቱ ሪኤጀንቶችን በማምረት እና መድኃኒቶችን በማቀነባበር ለሪኤጀንትና ለመድኃኒት ግዥ የሚወጣ የውጭ ምንዛሬ ሊቀንስ ይገባል፡፡ |
| | 6. ኢንስቲትዩቱ የሀገሪቱን የእንስሳት ጤና ለማስጠበቅ ጥራቱ፣ ደህንነቱና ፍቱንነቱ የተረጋገጠ የእንስሳት ክትባት በማምረት ለተጠቃሚ አካላት ሊያቀርብ ይገባል፡፡ |
| | 7. ኢንስቲትዩቱ የማምረት አቅም እያሳደገ በመሄድ ምርቱን ለተጠቃሚዎች በወቅቱ ተደራሽ ለማድረግ የሚያግዝ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፡፡ |
| | 8. ኢንስቲትዩቱ የሚያመርታቸው ክትባቶች በሀገሪቷ ውስጥ ያሉትን የበሽታ አምጪ ህዋስ /Strain/ ዝርያዎች ሙሉ ለሙሉ ያካተተ ሊሆን ይገባል፡፡ |

| የኦዲት ጭብጥ | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት |
| --- | --- |
| | 9. ኢንስቲትዩቱ በእንስሳት ጤና አጠባበቅ ረገድ ከባለድርሻ አካላት ጋር የጋራ ትብብርና የልምድ ልዉዉጥ መድረክ በማዘጋጀት ለተጠቀሚው አካላት የዕውቀት ሽግግር የሚያደረግበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 10. በእንስትቲዩቱ የተመረቱ የክትባት ምርቶች በበሽታ ላልተያዙ እንስሳት መደበኛ የሆነ ክትባት የሚከናወንበት ሥርዓት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 11. በእንስትቲዩቱ የሚመረቱ የክትባት ምርቶች የሀገር ዉስጥና የዉጭ ሀገር ፍላጎት ጋር የተጣጣመ ሊሆን ይገባል፡፡ |
| | 12. የክትባት ምርት እድገት ለማፋጠንና ለማስፋፋት ጥናትና ምርምር በማድረግ ነባር ክትባቶች ሊሻሻሉና አዳዲስ ክትባቶች ደግሞ ሊፈጠሩ ይገባል፡፡ |
| | 13. ኢንስቲትዩቱ የክልል ግብርና ቢሮዎች/ኤጀንሲ/ በሚያቀርቡት የክትባት ፍላጎት እቅድ መሠረት በወቅቱ የሚቀርብበትና አዳዲስ የክትባት ምርቶች ሲኖር መረጃው በወቅቱ የሚደርስበት የአሠራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 14. በኢንስቲትዩቱ የሚመረቱ የክትባት ምርቶች የሃገሪቱን ፍላጎት ሳያሟሉ ወደ ዉጭ አገር መላክ የለባቸውም፡፡ |
| ፬. የክትባት ማምረቻና የላብራቶሪ መሣሪያዎች፣ ሪኤጀንቶች፣ የክትባት | 15. ኢንስቲትዩቱ የተለያዩ ኬሚካሎች አያያዝ፣ አጠቃቀምና አወጋገድ እንዲሁም የተበላሹና ጊዜ ያለፈባቸዉ የክትባት ምርቶች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት በመሆን የአወጋገድ መመሪያ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ |

| የኦዲት ጭብጥ | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት |
|---|---|
| ምርቶች አያያዝና አጠቃቀም ውጤታማ ስለመሆኑ | 16. ክትባቶች ሲመረቱም ሆነ ከተመረቱ በኃላ የምርት ብክለትና ብክነት እንዳይኖር ኢንስቲትዩቱ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመነጋገር ለምርቱ ከሚፈልገው የኤሌክትሪክ ኃይል ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የኤሌክትሪክ ጉልበት ሊያገኝ የሚችልባቸውን አማራጮች እንዲዘጋጅ ሊያርግ ይገባል፡፡ |
| | 17. የክትባት ምርት ማምረቻ መሣሪያዎች ሲበላሹ ቶሎ ተጥግነዉ ወደ ስራ የሚገቡበት ሥርዓት ተዘረግቶ ተግባረዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 18. ኢንስቲትዩቱ እንደየሥራው ፀባይ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ የደንብ አልባሳት በወቅቱ ለሠራተኞች ሊያቀርብ ይገባል፡፡ |
| | 19. የክትባት ምርት ማምረቻ መሳሪያዎች አቅም ከክትባት ምርት ፍላጎት ጋር ሊጣጣም ይገባል፡፡ |
| | 20. በኢንስቲትዩቱ የአካባቢና የባለሙያ ደህንነት የሚጠብቅ የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 21. በምርት ክምችትና በክትባት አምራቾች ክፍል የክምችት መጠን መናበብ ሊኖር ይገባል፡፡ |
| | 22. የክትባቶች መጠን/ዶዝ/ ሲቀየር አብሮ የተጠቃሚዎች መመሪያ /የዩዘር ማኑአሎቹ/ ሊቀየሩ ይገባል፡፡ |
| | 23. ኢንስቲትዩቱ የሚጠቀምባቸው የማምረቻ እና ላብራቶሪ መሣሪያዎች ወቅታዊ የሆነ የክትትልና የልኬት (Callibration) ጊዜ ሊኖረውና በልኬቱ በሚሰጠው የማስተካከያ ሀሰብ መሠረት ሊያስተካክል ይገባል፡፡ |
| ፫..ኢንስቲትዩቱ ከባለደርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በመፍጠር የክትባት | 24. ኢንስቲትዩቱ የእንስሳት ክትባት ፖሊሲ እንዲዘጋጅና የህግ ሽፋን እንዲኖር ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 25. ኢንስቲትዩቱ ከክትባት ምርት ተጠቃሚ አካላት ጋር መደበኛ በሆነ |

| የኦዲት ጭብጥ | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት |
|---|---|
| ምርቶች ለተጠቃሚው የሚተዋወቁበት፣ ክትትልና ድጋፍ የሚደረግበት የአሠራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ስለማድረጉ መገምገም | መልኩ የሚገናኙበት መድረክ እና አዳዲስ ምርቶች ሲኖሩ የሚተዋወቁበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 26. ኢንስቲትዩቱ በክትባት አያያዝ እና አጠቃቀም ዙሪያ ለተጠቃሚዎች የግንዛቤ ማሰጨበጫ ሥራ የሚሰጥበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደረገው ይገባል፡፡ |
| | 27. ኢንስቲትዩቱ ለተጠቃሚዎች ክትባቱ በሚሰራጭበት አካባቢ በሚነገር ቋንቋ ግልጽ የሆኑ የክትባት አጠቃቀም መመሪያዎች አዘጋጅቶ ሊያሰራጭ ይገባል፡፡ |
| | 28. ኢንስቲትዩት ከእንስሳት አርቢው የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር የመረጃ ልውውጥ የሚያደርግበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 29. ኢንስቲትዩቱ በአገሪቱ ውስጥ ካሉት የእንስሳት የምርምር ማዕከላት ጋር ጠንካራ ግንኙነት በመፍጠር የክትባት አመራረት ቴክኖሎጂ ሽግግር ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 30. በኢንስቲትዩቱ የሚመረቱ ክትባቶች በእንስሳት ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ክትትልና ድጋፍ የሚደረግበት የአሠራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፡ |
| | 31. ኢንሰቲቲዩቱ የአመራረት እና የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ክፍተትን በመለየት ለባለሙያዎች ስልጠና የሚሰጥበትን ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 32. ኢንስቲትዩቱ የሚያመርታቸው የክትባት ምርቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆን ከዓለም አቀፍ የምርምርና ክትባት አምራች ተቋማት ጋር የልምድ ልውውጥ በማድረግ የአመራረት ዘዴውን ሊያሻሽል ይገባል፡፡ |

| የኦዲት ጭብጥ | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት |
|---|---|
| | 33. ኢንስቲትዩቱ በሚያመርታቸው የክትባት ምርቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪነቱን ለማስቀጠል የውጭ አገር የደንበኞች እርካታ የዳሰሳ ጥናት በማከናወን ምርታማነቱን ሊያሻሽል ይገባል፡፡ |
| | 34. ኢንስቲትዩቱ የታወቁት የእንስሳት በሽታዎችን በየአካባቢ በመለየት የበሽታ ፍንዳታ ከመከሰቱ በፊት በየዓመቱ ክትባቶች ሊሰጡ እንደሚገባ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ሊያከናውን ይገባል፡፡ |

## አባሪ 3፡ በኢንስቲትዩቱ የሚመረቱ የመከላከያ ክትባቶችና የሚሰጥበት የእንስሳት ዓይነት-

| ተ.ቁ | Scientific Name of the Vaccines | የክትባቱ ስም በአማርኛ | ክትባቱ የሚሰጥበት የእንስሳት ዓይነት |
|---|---|---|---|
| 1 | Antrax | አባ ሰንጋ | ለከብት፣ፈረስ፣በግና ፍየል |
| 2 | Bovine Pasteurellosis | የዳልጋ ከብት ጎሮርሳ | ለከብት |
| 3 | Ovine  Pasteurellosis | የበግ/ፍየል ጎሮርሳ | ለበግና ፍየል |
| 4 | Black Leg | አባ ጎርባ | ለከብት |
| 5 | Contagious Bovine Pleuropneumonia (CBPP) | የዳልጋ ከብት ሳንባ በሽታ | ለከብት |
| 6 | Contagious Caprine Pleuropneumonia (CCPP) | የፍየል ሳንባ በሽታ | ለፈየል |
| 7 | Pestedes pettis Ruminants (PPR) | የፍየል/በግ ደስታ መሰል በሽታ | ለበግና ፍየል |
| 8 | Sheep and Goat Pox (SGP) | የበግና ፍየል ፍንጣጣ | ለበግና ፍየል |
| 9 | Lumpy Skin Disease (LSD) | የጉርብርብ በሽታ | ለከብት |
| 10 | Foot and Mouth Disease (FMD) | የአፍታግር በሽታ | ለከብት/ለሚታለቡ |
| 11 | Afican Horse Sickness (AHS) | የአፍርካን ጋማ ከብት በሽታ | ለጋማ ከብት |
| 12 | New Castle HB1 | የዶሮ ፈንግል በሽታ/ለጫጩት | ለዶሮ |
| 13 | New Castle Lasota | የዶሮ ፈንግል በሽታ/ለመካከለኛና ትላልቅ | ለዶሮ |
| 14 | New Castle Thermostable | የዶሮ ፈንግል በሽታ ቤት ለቤት | ለዶሮ |
| 15 | New Castle –Oil Emulsion-in activated | የዶሮ ፈንግል በሽታ እንቁላል ጣይ | ለዶሮ |
| 16 | Fowl Pox | የዶሮ  ፈንጣጣ | ለዶሮ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 17 | Fowl Typhoid | **የዶሮ ሳልሞናላ መከላከያ** | **ለዶሮ** |
| 18 | Infectious Bursal Disease | **የዶሮ ጉንባሮ በሽታ** | **ለዶሮ** |
| 19 | Fowl Cholera | **የዶሮ ኀሮርሳ** | **ለዶሮ** |
| 20 | Mycoplasma Galisepticum (MG) | **የዶሮ ሳንባ በሽታ** | **ለዶሮ** |
| 21 | Camel Pox | **የግመል ፈንጣጣ** | **ለግመል** |
| 22 | Rabies | **የእብዱ ዉሻ በሽታ** | **ለዉሻ፣ድመት፣ቀበሮ** |

## አባሪ-4፡ የባለስልጣን መ/ቤቱ አሰራር ሥርዓት መግለጫ (System description/

